# የአርጐባ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ትንተና፡- *ክዋኔው፣ መዋቅሩ፣ ትዕምርቱና ፋይዳው*

እታገኘሁ አስረስ[1]፣ ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ኘሮፌሰር)[2]፣
የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)[3]፣ መሐመድ አሊ (ዶ/ር)[4]

## አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ የአርጐባ ብሔረሰብን የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ፣ መዋቅር፣ ትዕምርትና ፋይዳ መተንተን ነው፡፡ የአርጐባ ብሔረሰብ በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በሐረሪና በአፋር ክልሎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን (አህመድ 1999፡ 161) የዚህ ጥናት ትኩረት የአፋሩ አርጐባ ነው፡፡ ሥነ ስርዓት "አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርኣትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚሄድ ክንውን" (የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ 2006: 138) ነው፡፡ ክዋኔ የተግባቦት ስልት (Bauman 1975: 293)፣ መዋቅር የነገሮች ንዑሳን ክፍሎችና እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት (Storey 128)፣ ትዕምርት ሀሳብን የሚያስተላልፍ ቁስ፣ እንቅስቃሴና ግንኙነት (Geertz qtd.[5] in Turner 1997: 145) ሲሆን ፋይዳ ሥነ ስርዓቱ ለከዋኙ ማኅበረሰብ የሚሰጠው ጠቀሜታ ነው፡፡ በጥናቱ የቀደምት ጥናቶች ንባብና የመስክ ስራ ተከናውኗል፡፡ በመስክ መረጃ የተሰበሰበባቸው ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆኑ ዓላማ ተኮርና ጠቋሚ የናሙና ዘዴዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ መረጃን ለመተንተን ኢትኖግራፊ የጥናት ሞዴል ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ግኝት የብሔረሰቡ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ በመለየት፣ ሽግግርና መቀላቀል ሶስት ደረጃዎች ሊከፈል የሚችል መሆኑን፣ ድርጊታዊና (በቀኝ ማስተኛት፣ ጥልፍ መተርተር፣ ሽቶና ውሀ ማርከፍከፍ፣ ቅጠል መጐዝጐዝ፣ የሟችን ሚስት ቅቤ መቀባትና አዲስ ቀሚስ ማልበስ፣ ቆዳን በጠዋት ውሀ አርከፍክፎ ማጠፍ፣ በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ) ቁሳዊ (ውሀ፣ ቆዳ) ትዕምርቶች መኖራቸውን፣ ሥነ ስርዓቱ ተግባቦታዊና ማኅበራዊ (ለቅሶ መድረስ)፣ ኢኮኖሚያዊና (ሀፊሻ) ሥነ ልቡናዊ (በጋራ ማልቀስና ሶደቃ) ፋይዳዎች ያሉት መሆኑን አሳይቷል፡፡ ሀፊሻን ከዘመናዊ የመረዳጃ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር ለቀጣይነቱ አስተዋጽኦ ያደርጋል፤ ዚያራ[6]ም በጥልቀት ቢጠና መልካም ነው፡፡

ቁልፍ ቃላት፣ [አርጐባ፣ ለቅሶ፣ ሥነ ስርዓት፣ ክዋኔ]

---

[1] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፎክሎር ሶስተኛ ዲግሪ ዕጩ፣ የኢንታንጀብልና ኢትኖግራፊ ቅርስ ተመራማሪ I፣ ኢ-ሜይል አድራሻ etag907184@yahoo.com

[2] ጥናቱን ሲያማክሩ የነበሩ

[3] በቁሳዊ ባህል ረዳት ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤሜል አድራሻ yenfikirte2020@gmail.com

[4] በህገረሰባዊ ልማድ ረዳት ፕሮፌሰር፣ አማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኤሜል አድራሻ mohanebat@yahoo.com

[5] በሁለተኛነት ስሙ የተጠቀሰው ፀሐፊ መረጃውን ስሙ መጀመሪያ ከተጠቀሰው ፀሐፊ የወሰደው መሆኑን ለማመላከት ጥቅም ለይ የዋለ አጽርኦተ ቃል ነው፡፡

[6] የመታሰቢያ ሥነ ስርዓት ሲሆን ምንነቱ በጽሁፉ ወደፊት ተገልጿል፡፡

## 1. መግቢያ

ሥነ ስርዓት (Ritual) የፎክሎር አንድ ክፍል የሆነው ሀገረሰባዊ ልማድ ከሚይዛቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ሲሆን ቀዳሚ አላማው ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ ማሻገር የሆነ፣ መዋቅር ያለው፣ ተደጋጋሚና ትዕምርታዊ የሆነ ባህላዊ ድርጊት ነው (Davis-Floyd qtd. in Grimes 2000: 24)። የሥነ ስርዓት ዓይነቶች በርካታ ናቸው። ነገር ግን ይህ ጥናት የሥነ ስርዓት አንድ ፈርጅ ከሆኑ የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች አንዱ በሆነው በለቅሶ ሥነ ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።

የጥናቱ ዋና ዓላማ ከአርጎባ ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች መካከል የለቅሶ ሥነ ስርዓትን ከክዋኔ፣ ከመዋቅር፣ ከትዕምርትና ከፋይዳ አንፃር መተንተን ነው። በጥናቱ የአርጎባ ብሔረሰብ በለቅሶ ጊዜ የሚከውናቸው ሥነ ስርዓቶች ምን ምን ናቸው? እንዴት ይከወናሉ? የክዋኔዎቹ መዋቅር ምን ይመስላል? በክዋኔዎቹ ውስጥ ያሉ ሌሎች ፎክሎሮች ምን ምን ናቸው? በሥነ ስርዓቱ ውስጥ ያሉ ትዕምርቶች ምን ምን ናቸው? የሥነ ስርዓቱ ጠቀሜታ ምንድን ነው? የሚሉ የምርምር ጥያቄዎች መልስ አግኝተዋል።

የአርጎባ ብሔረሰብ በኢትዮጵያ አራት ክልሎች ማለትም በሐረሪ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራና በአፋር ክልሎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን (አህመድ 1999: 161) ይህ ጥናት በአፋር ክልል በሚኖረው የአርጎባ ብሔረሰብ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በአፋር ክልል የሚኖረው የአርጎባ ብሔረሰብ በክልሉ ዞን ሶስት፣ የአርጎባ ልዩ ወረዳ ውስጥ ይኖራል። ልዩ ወረዳው የአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ከአፋር ክልል ጋር በሚገናኝበት ድንበር ቦታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ በምዕራብ ሙሉ በሙሉ ከሰሜን ሸዋ ዞን የተለያዩ ወረዳዎች የሚዋሰን ሲሆን በምስራቅ ደግሞ በአብዛኛው ከአፋር ክልል የተለያዩ ወረዳዎች ጋር ይዋሰናል። ልዩ ወረዳው በስተምስራቅ ከአፋር ክልል ዱለቻ ወረዳ፣ በስተምዕራብ ከአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን አንኮበር ወረዳ፣ በስተሰሜን ከአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን ጣርማ በር ወረዳ እና በስተደቡብ ከአማራ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በረኸት ወረዳ ጋር የሚዋሰን ሲሆን በአስራ ሶስት ቀበሌዎች የተከፋፈለ ነው (የአርጎባ ልዩ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት 2010፡ 1-2)። ብሔረሰቡ የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ነው (አህመድ 1999፡ 16)።

የጥናቱ ትኩረት የሆነውን ብሔረሰብ እና ርዕሰ ጉዳይ ለመምረጥ ምክንያት የሆነው የመጀመሪያው ጉዳይ በተለያዩ አጋጣሚዎች የብሔረሰቡ ባህል በሌላ ባህል የተዋጠና ብሔረሰቡ በመጥፋት ላይ ያለ ተደርጎ ሲቀርብ (ለምሳሌ፣ Aklilu 2000፡ 173) ከመመልከቱ ጋር ይያያዛል። ብሔረሰቡ በመጥፋት ላይ ያለ ተደርጎ መታሰቡ ደግሞ የብሔረሰቡ ቋንቋ በመጥፋት አደጋ ላይ ከመሆኑ ጋር የተያያዘ ነው። በቦታው በምልከታ ማረጋገጥ እንደተቻለው በብሔረሰቡ ባህል የለውጥና ቀጣይነት ጉዳይ እንዳለ ሆኖ የብሔረሰቡ ቋንቋ የደረሰበትን አይነት የመጥፋት አደጋ በሌሎቹ የብሔረሰቡ የባህል እሴቶች፣ ሀይማኖትና ባህላዊ ልማዶች ላይ አልደረሰም። ባህላዊ ልማዶች በየመከወኛ አጋጣሚዎቻቸው ይከወናሉ። በመሆኑም ከንባብና ከቃል ምንጮች የተገኘው መረጃ በቦታው በመገኘት ከተገኘው መረጃ ጋር የተለያየ በመሆኑ ይህን ለማሳየት ብሔረሰቡና የጥናት ርዕሰ ጉዳዩ ለጥናት ተመርጧል። ሌላው ምክንያት የአርጎባ ብሔረሰብን የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች

በተመለከተ የተከናወነ ጥናት በተደረገው ፈርጀ ብዙ ደሰሳ ካለመገኘቱ ጋር የተያያዘ ሲሆን[7] ይህም የጥናት ርዕሰ ጉዳዩን ለመምረጥና በጉዳዩ ላይ ለመስራት ሌላኛው ምክንያት ሆኗል።

## 2. የጽንሰ ሀሳብ ማብራሪያ

Rappaport (1992፡ 24) ሥነ ስርዓት[8] የሚለውን ቃል "I take the term "ritual" to denote the performance of more or less invariant sequences of formal acts and utterances not entirely encoded by the performers" (አጽንኦቱ የእኔ ነው) በማለት በይነውታል። Rappaport እንደሚሉት ሥነ ስርዓት ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ከሞላ ጎደል የሆነ ወጥነት ያለው የመደበኛ እንቅስቃሴዎችና ንግግሮች ቅደም ተከተል ነው።

የተለያዩ ተመራማሪዎች ሥነ ስርዓትን በተለያየ መንገድ ከፍለዋል (ለምሳሌ፣ Shujaa 2009፡ 576; Sims and Stephens 2005፡ 114)። ነገር ግን Bell (1997: 93-129) የተሻለ መንገድ ነው ያሉትን የራሳቸውን የመከፈያ መንገድ አቅርበዋል። Bell ሥነ ስርዓቶቹ በጋራ የሚከወኑ፣ ልማዳዊና በተወሰነ መጠን በመለኮታዊ ፍጡራን ላይ ባለ እምነት ላይ የተመሰረቱ መሆናቸውን መመዘኛ በማድረግ ሥነ ስርዓቶችን በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የከፈሉ ሲሆን በአንድ ክፍል ካስቀመጧቸው ሥነ ስርዓቶች ውስጥ የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች (Rites of Passage) ይገኙባቸዋል።

የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች ከእርግዝናና ወሊድ ጀምሮ እስከ ሞት ድረስ ያሉ ዋና ዋና የሰው ልጅ ህይወት ሽግግሮችን ተከትለው የሚመጡ ሥነ ስርዓቶች ናቸው። በመሆኑም የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች የቦታ፣ የማኅበራዊ ደረጃና የእድሜ ለውጦችን ያጅባሉ (Barnard and Spencer 1996፡ 737; Feinberg 2004፡ 311)።

[7] ይህን ጥናት ለማከናወን የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ተደርጐ የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው የአርጐባ ብሔረሰብ ላይ ከዚህ ጥናት በተለየ ርዕሰ ጉዳይ የተከናወኑ ጥናቶች (እታገኘሁ አስረስ 2010; ሰይድ ሙሄ 2015; ዐቢዩ አስማማው 2005; አዲሱ ጴጥሮስ 2000; ተስፋዬ ኃይሉ 2000) እና የዚህ ጥናት ትኩረት በሆነው የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓት ርዕሰ ጉዳይ ነገር ግን በሌላ የጥናት አካባቢ የተከናወኑ ጥናቶች (ሥራዩ እንዳለው 2023; መሰለ ሙሉጌታ 2010; ኤልሳቤጥ ጥበቡ 2010; አበባ አማረ፣ ደስታ አማረና ፍሬህይወት ባዩ 2015; ድርብወርቅ ብፁ 2007; አፀደ ተፈራ 2007; ደስታ አማረ 2007; ለማ ንጋቱ 2006; ደስታ ወ/መስቀል 2006; ፍፁም ብርሃኑ 2006; ሥራዩ እንዳለው 2005; አየሁሽ ቶማ 2005; ውቤ ታደገ 2005; ዘላለም ፋንቱ 2004; ዝናሽ ሰለሞን 2004; ሕይወት አበሩ 2003; ሞገስ ሚካኤል 2002; መሰለ ሙሉጌታ 2000) የተገኙ ሲሆን ነገር ግን በአርጐባ ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች ላይ የተከናወነ ጥናት አልተገኘም።

[8] Leslau ባዘጋጁት የእንግሊዝኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት *Ritual* የሚለው ቃል "ሥነ ስርዓት" የሚል የአማርኛ አቻ ቃል ተሰጥቶታል (1973፡ 1087)። ሥነ ስርዓት የሚለው ቃል ደግሞ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት "አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርኣትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚሄድ ክንውን" የሚል ብያኔ ተሰጥቶታል (አጽንኦቱ የእኔ ነው) (2006፡ 138)። በመሆኑም በዚህ የጥናት ጽሁፍ Ritual የሚለው ቃል *ሥነ ስርዓት* በሚል አቻ የአማርኛ ስያሜ ቀርቧል።

የዚህ ጥናት ትኩረት ሞትን ተከትሎ የሚከወን የለቅሶ ሥነ ስርዓት ነው። Gerhart (2009: 1) እንደሚሉት ሞት ከህያዋንና ከመናፍስት ዓለም መካከል የቆመና ሁለቱን ዓለማት የሚለይ ሲሆን ሞትን ተከትለው የሚከወኑ ሥነ ስርዓቶችም በሁለቱ ዓለማት መካከል ያለን ግንኙነት መልክ ለማስያዝና በሀዘኑ የተጎዳን ቤተሰብና ማኅበረሰብ ቁስል ለማዳን ሲባል የሚከወኑ ናቸው። Lobar Youngblut and Brooten (2006፡ 44) እንደሚሉት ሰዎች የሟችን ነፍስ በተመለከተ ያላቸው እምነት የተለያዩ ሥነ ስርዓቶችን እንዲከውኑ የሚያደርጋቸው ሲሆን Gerhart (2009፡ 15) እንደሚሉት ደግሞ በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ አንድ ጊዜ ሞት ከተከሰተ በኋላ ተከትለው የሚመጡ ክዋኔዎች ከማኅበረሰቡ እምነትና ማኅበራዊ ልማድ የሚመነጩና ዋና ጉዳዮች ሲሆኑ በአብዛኛው እንደገና መወለድንና የነፍስ ሙት አለመሆንን መሰረት የሚያደርጉ ናቸው።

Pentikäinen (1997: 732-733) እንደሚሉት በህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች ከዋኔ የከዋኔው ዋና አቀንቃኝና ተሳታፊዎችም በማኅበራዊ ግንኙነታቸው ግልጽ የሆነ ለውጥን ያስተናግዳሉ። በተጨማሪም የለቅሶ ሥነ ስርዓት ዓላማ የሟችን አስከሬን፣ ነፍስና ሀዘንተኞችንም ማሻገር በመሆኑ ሟችና ቋሚዎች ማለትም የሟች ቤተሰብና ዘመዶች የጉዳዩ ቀጥተኛ ውጤት የሚያርፍባቸው ዋና ባለጉዳዮች ናቸው።

### 3. የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍ

የአርጐባ ብሔረሰብን የለቅሶ ሥነ ስርዓት ለመተንተን የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ፣ መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ፣ ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ እና ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውለዋል።

የክዋኔ ገለፃ በክዋኔ አላባውያን የእርስ በርስ ግንኙነት እና በእያንዳንዳቸው ምንነትና ትርጉም ላይ ትኩረት ያደርጋል። ክዋኔን ክዋኔ ከሚያስብሉ የክዋኔ አላባውያን መካከል ሰዎች ዋናዎቹ በመሆናቸው ከዋኞችና ታዳሚዎች በቅድሚያ የሚነሱ ናቸው። የክዋኔ ዘዴዎች ማለትም የድምጽ ክዋኔ፣ የሚታዩና ቁሳዊ ነገሮች፣ አካላዊ ገለፃዎችና በአካል መቅረብንና መራቅን በተመለከተ ያሉ ባህላዊ ደንቦችና ስሜቶች የክዋኔ ክፍሎች ሲሆኑ (Bauman 2012፡ 101) ከዋኞችና ታዳሚዎች፣ የክዋኔ ጊዜ፣ ቦታና አደረጃጀት የተለያዩ አይነት ክዋኔዎች እንዲኖሩ የሚያደርጉ ጉዳዮች ናቸው (Finnegan 1992: 89-91, 95)።

Dundes (qtd. in Bronner 2007፡ 123) መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብን ወደ ፎክሎር በማምጣት ሲበይኑት የፎክሎር መዋቅር ጥናት የእያንዳንዱ የፎክሎር ዘር ውስጣዊ ክፍሎች እርስ በእርስ ያላቸው ግንኙነትና አደረጃጀት የሚጠናበት ዘዴ መሆኑን ገልፀዋል። Gennep (1960) ሥነ ስርዓቶች በተለይም የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች ተከታታይ በሆኑ ሶስት ዋና ዋና የሽግግር ደረጃዎች የሚገለፁ ናቸው በማለት የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶችን መዋቅር ለይተዋል። Gennep ባቀረቡት የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶችን ለመረዳት የሚያስችል ሂደትን መሰረት ያደረገ ሞዴል የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች በሶስት ዋና ዋና የሽግግር ደረጃዎች ያልፋሉ ብለዋል። እነዚህ ደረጃዎች መለየት፣ ሽግግር እና መቀላቀል ናቸው። የመለየት ደረጃ ተሻጋሪው ግለሰብ ወይም ቡድን ቀደም ሲል ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር ከነበረው ማኅበራዊ ግንኙነት የሚለይበትና ወደሚቀጥለው

ደረጃ የሚሄድበት ነው። የሽግግር ጊዜ ከነባሩም ሆነ ከአዲሱ ማንነት ያልተደረሰበት፣ የተለየ ደረጃ የማይገኝበት የመካከለኛው ጊዜ ሲሆን የመጨረሻው የመቀላቀል ደረጃ ተሿጋሪው ሙሉ በሙሉ አዲስ በሆነ ማንነት ወደ ማኅበረሰቡ የሚመለስበት ነው።

Gennep (1960: 146, 147-153) በለቅሶ ሥነ ስርዓት ላይ የመለየት ጊዜ ከሽግግርና ከመቀላቀል ደረጃዎች በላይ ወሳኝ ተደርጐ የሚታሰብ መሆኑን በመጠቆም የመለየት ደረጃ ቀላል፤ የሽግግር እና የመቀላቀል ደረጃዎች ግን ረዥም የጊዜ ቆይታና ውስብስብ ሁኔታዎችን የያዙ መሆናቸውን ገልፀዋል። የሽግግር ጊዜ የሟች ነፍስ ወደ ሙታን ዓለም ለመቀላቀል ገና የሆነበት፤ የሟች ቤተሰብ አባላትም ከማኅበራዊ ኑሯቸው የሚለዩበት እንዲሁም የሟች አስከሬን በሀዘኑ ቤት ወይም በሌላ በተለየ ቦታ እንዲቀመጥ መደረጉ መገለጫው የሆነ ሲሆን የመቀላቀል ደረጃ የተለያዩ የለቅሶ ደንቦችና ክልከላዎች ማብቂያ ጊዜ ነው። ይህ ባለ ሶስት ደረጃ የሥነ ስርዓቶች ጥናት ሞዴል የአርጐባ ብሔረሰብን የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ ከመዋቅር አንፃር ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል።

Cohen (qtd. in Edith Turner 1997፡ 145) ትዕምርት የሚለውን ቃል ሲበይኑ ትዕምርት በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ በተመሳሰሎ መንገድ መልዕክት የሚያስተላልፉ፣ ሀሳብን የሚገልፁ፣ ለተለያዩ ትርጉሞች የቆሙና የተለያዩ ስሜቶችን የሚገልፁ ቁሶች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ድርጊቶች፣ ሀሳቦች፣ ቃላትና ግንኙነቶች ሁሉ መጠሪያ መሆኑን ገልፀዋል። Turner (1975: 166) ማመሳሰልና ማዛመድ የብዙ ትዕምርቶችን ፍች የሚገዛ መርህ በመሆኑ የትዕምርት ፍቺም ሶስት መሰረቶችን በማመሳሰልና በማዛመድ ይመሰረታል ብለዋል። እርሳቸው እንደሚሉት ሶስቱ ፍች የሚገኝባቸው አላባውያን የትዕምርቱ ስያሜ፣ የትዕምርቱ አካላዊና ሥነ ህይወታዊ ምንነትና ትዕምርቱ ያለው ቁሳዊ ገጽታ ናቸው።

ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ (Functionalism) በፎክሎር ጥናት እያንዳንዱ የፎክሎር አሀድ ተግባር ሊኖረው ይገባል፤ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ ወይም ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ሊያበረክት ይገባል የሚል መነሻ ያለው ነው (Malinowski 159; Bell 1997፡ 23)። ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ማኅበራዊ ለውጦችን አይመለከትም የሚል ትችት የቀረበበት ሲሆን ይህን አስመልክቶ Radcliffe-Brown (1952፡ 185) የንድፈ ሀሳቡ ትኩረት ተቋማት በማኅበራዊ ስርዓት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ መለየት እንጂ በጊዜ ሂደት እንዴት ተለወጡ የሚለውን መመርመር አይደለም፤ ሁለቱ የተለያዩ ጥናቶች ናቸው ብለዋል።

የአርጐባ ብሔረሰብን የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ ውስጥ ያሉ አላባውያንን ምንነትና እርስ በርስ ያላቸውን ግንኙነት ለመለየት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። ምንም እንኳን መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብ በቅርጽና ሂደት ላይ እንጂ በማኅበራዊ ፋይዳ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ባያደርግም በዚህ ጥናት የክዋኔን አደረጃጀትና ክፍሎች ለመለየት ዓላማ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል። በክዋኔው ውስጥ ለተለዩ ትርጉሞች የቆሙ ቁሶችን፣ እንቅስቃሴዎችን፣ ድርጊቶችን፣ ሀሳቦችን፣ ቃላትንና ግንኙነቶችን ለመለየት ትዕምርታዊ ንድፈ ሀሳብ ጥቅም ላይ ውሏል። ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ ከፍ ሲል እንደተገለፀው መዋቅራዊ ንድፈ ሀሳብን በመጠቀም ተመርምሮ የማይገኘን የነገረ ፋይዳን ጉዳይ ለመመርመርና ሥነ ስርዓቱ ለከዋኞቹ ግለሰቦችና በአጠቃላይ ለማኅበረሰቡም ምን አይነት ፋይዳዎች

አሏቸው የሚለውን ለመለየት ጥቅም ላይ ውሏል። ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ የለውጥን ጉዳይ ችላ ይላል የሚል ትችት ቢኖርበትም በዚህ ጥናት ጥቅም ላይ የዋለው ለውጥን በማንፀሪያነት ሳይሆን የሥነ ስርዓቱ ክዋኔ ለከዋኙ ማኅበረሰብ የሚሰጠውን ፋይዳ በመመርመሪያነት ነው።

## 4. የአጠናን ዘዴ

ይህን ጥናት ለማከናወን በቃላት፣ በገለፃዎች፣ በሀሳቦች፣ በስሜቶች የተገለፀ መረጃ ያስፈልጋል። ይህንን መረጃ ለማግኘት የጥናት ርዕሰ ጉዳዩንና አካባቢውን በተመለከተ የተከናወኑ ጥናቶችን በማንበብና የመስክ ስራ በማከናወን መረጃ ተሰብስቧል። የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የአርጐባ ብሔረሰብ በልዩ ወረዳው በሚገኙ 13 ቀበሌዎች ውስጥ የሚኖር ሲሆን ዓላማ ተኮር የናሙና ዘዴን በመጠቀም ጥናቱ በተመረጡ አምስት ቀበሌዎች ማለትም በጋቸኔ፣ በገበሮች፣ በላይ መጠቅለያ፣ በጨኖና በአባሊ ቀበሌዎች ውስጥ ተከናውኗል።

መረጃ የተሰበሰበበትን የመስክ ጊዜ በሶስት[9] ከፍሎ መመልከት ይቻላል። የመጀመሪያው የመስክ ስራ ከ1/10/2012 ዓ.ም. እስከ ከ30/12/2012 ዓ.ም. ድረስ በመመላለስ የተከናወነ ሲሆን ሁለተኛው የመስክ ስራ ከ1/2/2013 ዓ.ም. እስከ 30/7/2013 ዓ.ም. በተመሳሳይ በመመላለስ የተከናወነ ነው። ቀጣዩ የመስክ ስራ የጥናት ጽሁፉ ከተዘጋጀ በኋላ ወደ አካባቢው በመሄድና ለቁልፍ የመረጃ ሰጪዎች በማቅረብ መረጃዎች በትክክል መተርጐማቸውን ለማረጋገጥ የተደረገ የጥቂት ቀናት የመስክ ስራ ነው። በመሆኑም ይህ የጥናት ጽሁፍ በእነዚህ የመስክ ጊዜዎች በተሰበሰበ መረጃ የተዘጋጀ ነው።

በመስክ መረጃ የተሰበሰበባቸው ዘዴዎች ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ናቸው። ምልከታ በዋና መረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን በምልከታ ያልተገኘን መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ ጥቅም ላይ ውሏል። መረጃን ለማጣራትና ለማጠናከር ቡድን ተኮር ውይይት ተከናውኗል። ምልከታ የተከናወነው በተፈጥሯዊ አውዶች ነው። በመሆኑም 1 የሀፈሻ ሥነ ስርዓት፣ 2 የቀብር ቀን ሥነ ስርዓቶች ማለትም የመሸኛ ዝግጅት፣ የስራ ክፍፍል፣ የአለቃቀስ ሥነ ስርዓት፣ ወዘተ፣ 1 አስከሬን የማጠብና የመገነዝ ሥነ ስርዓት፣ 1 የቆዳ ማጠፊያ፣ 1 የወርና 1 የዓግል መፍቻ ሥነ ስርዓቶች ላይ ምልከታ የተደረገ ሲሆን በተወሰኑ ክዋኔዎች ውስጥ ተሳትፏዊ ምልከታ ተደርጓል። ሀይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ሴት በቀብር ሥነ ስርዓት ላይ እንድትገኝ የማይፈቀድ በመሆኑ በቀብር ሥነ ስርዓት ላይ በመገኘት ምልከታ ለማድረግ አልተቻለም፤ ክዋኔውን በተመለከተ የመረጃ ክፍተት እንዳይኖር የቃለመጠይቅ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል። በመሆኑም ከፊል ነፃ እና ነፃ ቃለመጠይቆችን በመጠቀም በዓላማ ተኮርና ጠቋሚ የናሙና ዘዴዎች ለመረጃ ሰጪነት ለተመረጡ 33 ሰዎች ቃለመጠይቅ በማድረግ መረጃ ተሰብስቧል። በዚህ ጥናት መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ቡድን ተኮር ውይይቶች በመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን በመደበኛው ቡድን ተኮር ውይይት ከአምስት እስከ አስር ተወያዮች የተሳተፉባቸው አምስት ቡድን ተኮር ውይይቶች ተደርገዋል። በተጨማሪም ከላይ እንደተገለፀው ከማኅበረሰቡ አባላት ጋር በነበረኝ ቆይታ በተገኘሁባቸው

[9] ይህ የጥናት ጽሁፍ የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት ክፍል ነው።

ውይይቶች የጥናት ርዕስ ጉዳይ የሆኑ ነጥቦች ሲነሱና ሆን ብሎ በማንሳትም በአካባቢው ያሉ ሰዎች ሀሳባቸውን እንዲሰጡ በማመቻቸት መደበኛ ባልሆነ መንገድ መረጃ ተሰብስቧል።

በመስክ የተሰበሰበውን መረጃ ለመቅረጽ ጥቅም ላይ የሉ የመቅረጫ መሳሪያዎች መቅረፀ ድምጽ፣ የመስክ ማስታወሻ፣ የቪዲዮ ካሜራና የፎቶግራፍ ካሜራ ናቸው። በመቅረፀ ድምጽ የተቀዱ መረጃዎች በየእለቱ ወደ ኮምፒውተር ተገልብጠው መረጃዎቹ የተገኘበት ቦታ፣ ቀን፣ ወዘተ ተመዝግቧል። ቁልፍ ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም የተያዙ ማስታወሻዎችን በመስክ ውሎ መጨረሻ ላይ በተብራራ መልኩ በሌላ ማስታወሻ በመፃፍና ማስታወሻ የተያዘበትን ቦታና ቀን በመመዝገብ የመረጃውን ይዘት በሚጠቁም አንድ ቃል ተደራጅቷል። በቪዲዮና በፎቶግራፍ ካሜራዎች የተቀረፁ መረጃዎችን በየእለቱ ወደ ኮምፒዩተር በመገልበጥ መረጃው የተገኘበት ቦታና ቀን ተመዝግቧል። መረጃው በጽሁፍ ወደሰፈረው መረጃ ተደባልቋል፤ የመረጃ ክፍተትን ሞልቷል፣ አጠናክሯል። የፎክሎር ጥናት መስክ ማኅበረሰብን ከሚከውነው ፎክሎር በመነሳት መረዳት የሚያስችል በመሆኑ በመረጃ መሰብሰብ ስራ ወቅት ውስጣዊ አንፃርን በመጠቀም መረጃው በታየበትና በተሰማበት መንገድ፤ የማኅበረሰቡ እውነታ ከራሱ ከማኅበረሰቡ አንፃር ማኅበረሰቡ እንዳለው ቀርቧል። ውጪያዊ አንፃርን በመጠቀም ደግሞ የተሰበሰበው መረጃ ከሳይንሳዊ ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች አንፃር ተተንትኗል።

## 5. የአርጐባ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ፣ መዋቅርና ትዕምርት

በዚህ ክፍል የአርጐባ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ Gennep (1960) የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች ያልፉባቸዋል ካሏቸው የመለየት፣ የሽግግርና የመቀላቀል ደረጃዎች አንፃር ቀርበዋል፤ ትዕምርታዊ ጉዳዮች ተለይተው ፍካሬያዊ ፍቺዎቻቸውም ቀርበዋል።

### 5.1. መለየት

በአርጐባ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ የመለየት ደረጃ ሰው በጠና ሲታመም ጀምሮ ሞት እስኪከሰት ድረስ ያለውን ጊዜ ይይዛል። ከህመም እስከ ሞት ባለ ጊዜ የሚከወኑ ሥነ ስርዓቶች የመለየት ጊዜ መገለጫዎች ናቸው።

በአርጐባ ብሔረሰብ አንድ ሰው ሲታመም ቤተሰቡ፣ ዘመዶቹና ጐረቤቶቹ ሁሉ እንደየቅርበታቸው ሁኔታ ያስታምሙታል፤ ይረዱታል። ህመምተኛው የሚያምረውና የሚፈልገው ምግብ እየተጠየቀ ይዘጋጅለታል። ህመምተኛው እየደከመ ሄዶ ምግብ መብላት የሚያቅተው ደረጃ ከደረሰ ደግሞ ውሃ በስኒ ተደርጐ በንድፍ ጥጥ እየተነከረ አፉ ላይ እየተጨመቀለትና ከንፈሩ እየተጠራረገለት ይቆያል (ወ/ሮ ከድኝ መሐመድ ሰዒድ፣ 4/5/2013፣ ገቀ[10]፣ ቃመ[11])[12]። ውሃ ህይወትን፣ መለምለምን፣ መቀጠልን፣ መሻገርን ይወክላል። ህመምተኛ ሲደክም በጥጥ በተነከረ ውሃ አፉ እየተጠራረገለት

---

[10] ገበሮች ቀበሌ

[11] ቃለመጠይቅ

[12] ቀዳማይ መረጃ መረጃውን ከሰጠው ሰው ስም፣ መረጃው ከተገኘበት ቀንና ቦታ እንዲሁም መረጃው ከተሰበሰበበት ዘዴ አንፃር በዚህ መልኩ ሰፍሯል።

መቆየቱ ህመምተኛው ለሞት ሊዳርገው ከሚችል ህመሙ እንዲሽርና ህይወቱ እንዲቀጥል፣ ህመምተኛው እንዲለመልም እንጂ እንዳይደርቅ፣ ህይወቱ እንዲቀጥል እንጂ እንዳይቋረጥ፣ ህመሙን እንዲሻገረው እንጂ በህመሙ እንዳይቀር ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

ህመምተኛው ህመሙ ሲፀናም በቀኝ ጐኑ እንዲተኛ ይደረጋል (ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ፣ 22/2/2013፣ ጋቀ[13]፣ ቃመ)። በብሔረሰቡ ዘንድ ቀኝ የገድ ተምሳሌት፣ የመልካም ዕድል፣ የሰማያዊ ሀሳብ ተምሳሌትና ብሩህ የሆነ መፃዒ ጊዜን መመኛ ሲሆን በአንፃሩ ግራ የአንጋዳ፣ የመጥፎ እድልና የእርኩስ መንፈስ መገኛ ተደርጐና ከሞት በኋላም ጀነት የቀኝ፣ ጀሀነም ደግሞ የግራ እንደሆኑ ስለሚታመን የታመመን በቀኝ ጐኑ የማስተኛት ድርጊት ታማሚው ከህመሙ እንዲድን፣ መልካም እንዲሆንለት፣ ቢሞት እንኳን የጀነት እንዲሆን ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

ወ/ሮ እመይ መሐመድ ነጋሽ (22/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ) እንደገለፁት ሰው ታሞ ህመሙ ለሞት ያሰጋዋል ተብሎ ሲታሰብ ሰው ተጠርቶ ዱዓ ይደረግለታል። ዱዓው ምህረትን ያስገኝለታል ወይም ጣሩን ያሳጥርለታል ተብሎ ይታመናል። ህመምተኛው ለሞት የሚያሰጋው መሆኑን የሚጠቁሙ ምልክቶች በዋናነት የሰውነት መዛል፣ መናገር አለመቻል ወይም የአንደበት መያዝ፣ በትኩረት ማየት አለመቻል ወይም አይኑ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ መመልከት፣ ራስን መሳትና የሰውነት ከእግር ጀምሮ ወደ ላይ እየቀዘቀዘ መሄድ ናቸው። የህመምተኛው የአተነፋፈስ ሁኔታም ህመምተኛው ያለበትን ሁኔታ ይጠቁማል። በአርጐባዎች እምነት መሰረት ሰው ሲሞት ነፍሱ ከሆድ ተነስታ ወደ ደረት፣ ከዚያም ወደ ጉሮሮ ከፍ በማለት በመጨረሻም በአፍንጫ ትወጣለች። ነፍስ ከሆድ ተነስታ ወደ ደረትና ጉሮሮ መሄዷ በየቦታው በሚሰማው የኩርፍርፍታ ድምጽና የአተነፋፈስ ሁኔታ ይለያል። የታመመ ሰው እነዚህ ምልክቶች ሲታዩበት ነፍስ የምትወጣበት ጊዜ ስለማይታወቅ ቤተሰብ የሆነና የቅርብ ሰው አጠገቡ ቁጭ ብሎ ይጠብቀዋል። አንድ ሰው ነፍሱ እንደወጣችና እንደሞተ ሲረጋገጥ አጠገቡ ያለ ሰው ያካትመዋል[14]።

የመለየትን ጊዜ መገለጫ ከሟችና ከሟች ቤተሰብ አንፃር መመልከት ይቻላል። ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች ከመሞቱ በፊት በጠና ሲታመም ከሌላው ሰው ተለይቶ ይታያል። በመሆኑም ሰዎች የቅርበታቸውን ያህል ያስታምሙታል፣ ይንከባከቡታል፣ የሚያምረውን ምግብ እየጠየቁ ያዘጋጁለታል፣ ፍየል ያርዱለታል፣ ዱዓ ያደርጉለታል፣ አንድ ሰው ከራስጌው ቁጭ ብሎ የፈጣሪን አንድነትና የዓለምን ጠፊነት እየነገረ በልቦናው እንዲያሳድር ይረዳዋል። ታማሚው ሰው ነፍሱ ከስጋው ሲለይም ከገሀዱ ዓለም ኑሮ ይለያል። ይህ ደረጃ ከሟች ቤተሰብ አንፃር ሲታይ የሟች ቤተሰብ አባላት ሀዘንተኞች በመሆናቸው ከቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴያቸውና ከማኀበራዊ ኑሯቸው የሚለዩበት ነው።

---

13 ጋቸኔ ቀበሌ

14 የሟችን ዓይንና አፍ በመዳፍ በመያዝ እንዲዘጋ ማድረግ

## 5.2. ሽግግር

በአርጐባ የለቅሶ ሥነ ስርዓት የሽግግር ጊዜ ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት እስከሚከወንበት ቀን ዋዜማ ድረስ ያለውን ሰፊ ጊዜ ይሸፍናል። የሽግግር ጊዜ መገለጫዎች ከሞት በኋላ ጥሪ ከማድረግ ጀምሮ የዳስ መጣል፣ የመሸኛ ማዘጋጀት፣ የመቃብር ጉድጓድ የመቆፈር፣ አስከሬን የማለስለስ፣ አስከሬን የማጠብና የመገነዝ፣ በጋራ የማልቀስ፣ በቀብሩ ቀን በሀዘኑ ቤት በጋራ የመመገብ፣ አስከሬን የማጓጓዝ እንዲሁም የቀብርና የሀፈሻ[15] ሥነ ስርዓት ክዋኔዎች ናቸው።

### 5.2.1. ጥሪ ማድረግ

በአርጐባዎች ዘንድ ሰው ሲሞት ቤተሰቡና አብሮ የነበረ ወዳጅ ዘመድ ወጥቶ በደጅ ስለሚያለቅስ በቅርብ ያለ ሰው ሲለቀስ በመስማትና እርስ በእርሱ በመነጋገር ሀዘኑን ሰምቶ ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ እርሙን ያወጣል። ሞት የተከሰተው በቀን ከሆነ የቀብር ሥነ ስርዓቱም በዚያው ቀን የሚከናወን በመሆኑ ሰዎች በሀዘኑ ቤት ተገኝተው የቀብር ዝግጅት እንዲያደርጉ ስለሚፈለግ ጐረቤቶች ሀዘኑን ላልሰሙ ሌሎች የአካባቢው ሰዎችና እድር ያለበት አካባቢ ከሆነ ለእድር ይነግራሉ። ሞት የተከሰተበት ሰዓት ምሽትና ሌሊት ከሆነ ግን የቀብር ሥነ ስርዓቱ የሚከናወነው በማግስቱ በመሆኑና በዋዜማ ምንም የቀብር ዝግጅት ስለማይደረግ የሰማው ሰው ብቻ ያለቅስና የሞቱን ዜና ለሌሎች የማድረስና ለእድር የመንገር ስራ የሚከናወነው ሲነጋ ተጠብቆ በማለዳ ነው። የለቅሶ መልዕክትና ጥሪ ሩቅ ላለ ዘመድና ወዳጅ የሚነገረው በሁለት መንገድ ነው። አንደኛው መንገድ "ኸረን" ሲሆን ሰዎች ከፍ ያለ ቦታ ላይ በመሆን ራቅ ያለ አካባቢ ላሉ ሰዎች ጮክ ብለው ጥሪ በማድረግ ሀዘን መድረሱን መልዕክት የሚነግሩበት መንገድ ነው። ሁለተኛው መንገድ ሰዎች በቅሎ ተጭኖላቸው በቦታው ሄደው የሚነግሩበት መንገድ ነው (ወ/ሮ ሶሀሊየት ባቢ፣ 29/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

### 5.2.2. ዳስ መጣል

በቀብሩ እለት ጠዋት ወንዶች ለእንግዳ መቀበያና ለምግብ ማዘጋጃ የሚሆን ዳስ ይጥላሉ። መቀመጫ እንዲሆን ቅጠል የሚጐዘጐዝ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ውስጥ መዋስ ይነጠፋል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም[16])። በለቅሶ ሥነ ስርዓት ላይ ዳስ መጣል ሞት ምን ያህል ሰዎችን የሚያሰባስብና የማኅበረሰብን አንድነት የሚያጠብቅ መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርት ነው። ሰዎች በለቅሶ ጊዜ በአንድ ዳስ ውስጥ በአንድ ላይ መሰብሰባቸው የተከሰተው ሞት ያስከተለባቸውን የጋራ የሀዘን ስሜት በጋራ ሆነው ለመቋቋም መነሳታቸውን ያሳያል። መዋስ በተነጠፈበት ቤት ውስጥ ሞት መከሰቱንና ለቅሶ መሆኑን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ቁስ ነው። በብሔረሰቡ ዘንድ "መዋስ ዘርግታለች" ማለት ለቅሶ ተቀምጣለች የሚል መልዕክትን ያስተላልፋል።

---

[15] ጐረቤቶች ከቀብር ቀን በኋላ ባሉ ስድስት ቀናት ማታ ማታ ምግብ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑበት ሥነ ስርዓት

[16] ምልከታ

### 5.2.3. መሸኛ ማዘጋጀት

መሸኛ በቀብሩ እለት ለቀባሪና ለለቅሶ ደራሽ የሚቀርብ ምግብና መጠጥ ሲሆን የሚዘጋጀው የቀብር ሥነ ስርዓቱ በሚከናወንበት እለት ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 14/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። በእለቱ በሀዘኑ ቤት ምግብ ለማዘጋጀት የሚውል ግብዓት ከሌለ ይዘጋጃል ወይም ሴት ጎረቤቶች ከየቤታቸው በማምጣት እንጀራ ይጋግራሉ፤ ወጥ ይሰራሉ፣ ንፍሮ ይቀቅላሉ፤ ቡናና ሻይ ያፈላሉ። ሴቶች ጋገራውን፣ ወጥ መስራቱንና ቡናና ሻይ ማፍላቱን የሚያከናውኑ ሲሆን ወንዶች እርድ የሚደረግ ከሆነ እርዱን በማከናወን ስጋውን ቆራርጠው ለሴቶች ያስረክባሉ፣ ንፍሮ ይቀቅላሉ፣ ማገዶ ያቀርባሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)። ከመሸኛው አንዱ ቦላ[17] ነው (ወ/ሮ አሚና ኢብራሂም፣ 14/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

### 5.2.4. የመቃብር ጉድጓድ መቆፈር

ሰው ሞቶ የቀብር ሥነ ስርዓቱን ሊያዘገይ የሚችል ምክንያት ከሌለ በተቻለ ፍጥነት የቀብር ጉድጓድ ቁፋሮው ይጀመራል (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)። የቀብር ጉድጓድ መጀመሪያ ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ሶስት ክንድ ቁመት፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ ደግሞ ሁለት ክንድ ጐን እንዲኖረው ተደርጐ በዶማ ወደ ታች ይቆፈራል። ወደ ታች የሚቆፈረው መጠን መካከለኛ ቁመት ያለው ሰው ቆሞና እጁን ወደ ላይ ዘርግቶ የጉድጓዱን አፍ መንካት እስኪችል ድረስ የሚሆን ጥልቀት እንዲኖረው ተደርጐ ነው። ይህን ያህል ጥልቀት ከተቆፈረ በኋላ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ለአስከሬኑ መቅበሪያ የሚሆን የመቃብር ክፍል ወይም ለኸድ ወደ ጐን ይቆፈራል። ይህ ጉድጓድ በሩ አስከሬን ለማስገባት የሚያስችል፣ ጐኑ አስከሬን ለማስተኛት የሚያስችልና ቁመቱም ሰው ሊያስቀምጥ የሚችል ተደርጐ ይቆፈራል። ቁመቱና ጐኑ ልክ ሲሆን ውስጡን ጥሩ አድርገው በመጥረቢያ ያለሰልሱታል (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)።

ከሟች ዘመዶች መካከል በእድሜ አንጋፋ የሆነ ሰው በመቆፈሪያ መሬቱን ቆፈር አድርጐ ከጀመረ በኋላ ቆፋሪዎች ይቀበሉትና ጉድጓዱ እየተቆፈረ ሌሎች ደግሞ ለኸዱ የሚዘጋበትን ድንጋይ ያመጣሉ። ጉድጓዱን የሚቆፍሩ ሰዎች የሟች ወዳጅ ዘመዶችና ጐረቤቶች የሆኑ ወንዶች ናቸው (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)።

ከመቃብር ስፍራዎች ላይ ዛፍ መቁረጥ ክልክል ነው (አቶ ኑርዬ በሺር፣ 4/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)። ሰማያዊው ጀነት ለምለምና በተክሎች የተሞላ፣ ቀዝቃዛና ነፋሻማ አየር ያለው እንደሆነ ይታመናል። ይህም ድርጊት የመቃብር ስፍራዎች አረንጓዴና ቀዝቃዛ እንዲሆኑ ተደርገው ለሙታን ጥሩ አየር እንዲያስገኙ፣ ለምለም ወደ ሆነው ጀነትም እንዲመሯቸው በማሰብና ለማምሰል የተደረገ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

[17] በቀብር እለት ለቀባሪ የሚታደል ጥሬ ስጋ

### 5.2.5. አስከሬን ማለስለስ

አስከሬን ለስልሶ ቆይቶ በአጠባና በቀብር ጊዜ የገራ እንዲሆን ስለሚፈለግ እስኪገነዝ ድረስ ባለው ሰዓት ሁሉ አስከሬን የማለስለስ ስራ ይሰራል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ *ጋቀ፣ ቃመ*)። የመጀመሪያው የማለስለሻ መንገድ የቀብሩ ሰዓት ደርሶ አስከሬኑ እስኪገነዝ ድረስ የእጣን ዛፍ ቅጠል ጉዝጉዞ አስከሬኑን እዚያ ላይ ማስተኛትና ጭንቅላቱን ወደ ቀኝና ወደ ግራ እያንቀሳቀሱና የእጅና የእግር መገጣጠሚያውን እያጠፉና እየዘረጉ መቆየት ነው። ዋናው መንገድ አስከሬኑ እስኪታጠብ ድረስ ያለመታከት አጠገቡ ሆኖ መገጣጠሚያውን ሁሉ እያጠፉና እየዘረጉ መቆየት ሲሆን የእጣን ዛፍ ቅጠሉ የማለስለስ ባህርይ ስላለው አስከሬኑ በቀላሉ እንዳይደርቅ ያደርገዋል ተብሎም ይታመናል። ነገር ግን ይህን የሚያደርግ ጠፍቶ በአጋጣሚ አስከሬኑ ቢጠነክር አብሽ፣ የእምቧይ ስር፣ የጥድ እንጨት ወይም የባህር ዛፍ ቅጠል አስከሬኑ ካለበት አልጋ ስር ተደርጐ ይጨሳል። እነዚህ ጭሶች አስከሬን የማለስለስ ባህርይ እንዳላቸው ይታመናል። ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬኑን የሚያለሰልሰው ወንድ ሲሆን ሟቿ ሴት ከሆነች ደግሞ የማለስለስ ስራ የምትሰራ ሴት ነች። ነገር ግን አስገዳጅ ሁኔታ ሲፈጠርና ሰዎች እስኪመጡ ድረስ ወንዱ የሴት ቤተሰቡን አስከሬን፤ ሴቷም የወንድ ቤተሰቧን አስከሬን ማለስለስ ይችላሉ (አቶ አብዱልቃድር ቃሲም፣ 7/3/2013፣ *ላመቀ፣ ቃመ*)።

### 5.2.6. አስከሬን ማጠብና መገነዝ

አስከሬን የሚገነዘው የመቃብር ጉድጓድ ቆፋሪዎች ቁፋሮው ሊያልቅላቸው የሚችልበትን ሰዓት በመገመት አስከሬኑን አስተካክላችሁ ለዚህ ሰዓት አድርሱልን ብለው በሚልኩት መልዕክት መሰረት ነው። መልዕክቱ እስኪላክ ድረስ አስከሬኑን ለማጠብና ለመገነዝ የሚያስፈልጉ ነገሮች ተዘጋጅተው አስከሬኑ እየተለሰለሰ የሚቆይ ሲሆን መልዕክቱን የሚነግር ሰው ሲላክ አስከሬኑ በአግባቡ ታጥቦ ይገነዛል (20/2/2013፣ *ጋቀ፣ ም*[18])።

**አስከሬን ማጠብ፣** አስከሬን ለማጠብ የሚያስፈልጉ የቁርቁራ ውሃ፣ ንፁህ ውሀና ሳሙና ናቸው። የቁርቁራ ውሃ የሚዘጋጀው መጀመሪያ የቁርቁራ ዛፍ ቅጠሉ እየተለቀመ በሳፋ ላይ በተደረገ ውሀ ውስጥ ይጨመርና አረፋ እስኪወጣና ውሀውም አረንጓዴ እስከሚሆን ድረስ ታሽቶ ውሀው በንፁህ ወንፊት ተጠልሎ በዕቃ ይቀመጣል (20/2/2013፣ *ጋቀ፣ ም*)።

አስከሬን የሚታጠበው መጀመሪያ ጉድጓድ ይቆፈርና በጉድጓዱ ላይ ሁለት ትልልቅ እንጨት ወይም ጣውላ ተጋድሞ አስከሬኑ ሳይጋለጥ እስከተሸፈነበት ጨርቅ ከቆየበት አልጋ ላይ ተነስቶ እዚያ ላይ ይደረጋል። ጉድጓዱ የሚቆፈረው የሚፈሰው ውሀ የትም እንዳይሄድና በጉድጓዱ ውስጥ ገብቶ እንዲሰርግ ለማድረግ ነው። ከዚያ በኋላ አስከሬኑን ቁጭ በማድረግ ሁለት ሰው ትከሻውንና አንድ ሰው ጭንቅላቱን ደግፎ በመያዝ ሌላ ሰው ደግሞ የአስከሬኑን ሆድ ጫን ጫን በማድረግና በማሸት

[18] ወ/ሮ እመቤት ይኖሩበት ከነበረው አባሊ ቀበሌ ህክምና ለማግኘት ጋቸኔ ወደምትኖረው ልጃቸው ወ/ሮ ዘሀራ ሀሰን መጥተው በ16/3/2013 እዚያው አርፈዋል። ፈቃድ ተገኝቶ አስከሬን ሲታጠብና ሲገነዝ ምልከታ ተደርጓል።

በሆድ ዕቃው ውስጥ ቆሻሻ ካለ እንዲወጣና ሆድ ዕቃው ንፁህ እንዲሆን ያደርጋሉ። ከዚያ በኋላ እጃቸውን በሽማ ጠቅልለው አካባቢውን በውሃ ካፀዱ በኋላ አስከሬኑን አስተኝተውና እጃቸውን ታጥበው ከላይ የተሸፈነበት ጨርቅ ሳይነሳ አስከሬኑን ማጠብ ይጀምራሉ (20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

መጀመሪያ አስከሬኑ በውሀና በሳሙና ይታጠብና ሲያበቃ በቅደም ተከተል ተዘጋጅቶ በተቀመጠው የቁርቁራ ውሃና በንፁህ ውሃ ይታጠባል። በዚህ ጊዜ አስከሬኑ በኡዱ መልክ ይታጠባል። አስከሬኑ ሲታጠብ መጀመሪያ ከቀኝ ጐን ያሉት ቀኝ ጐኑን፣ ቀኝ እጁንና ቀኝ እግሩን ያጥባሉ፣ ከዚያ በኋላ ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ በስተግራ ያሉት ሰዎች የበስተግራ በኩሉን ያጥባሉ (20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)። በብሔረሰቡ ዘንድ ቀኝ የመልካም እድል፤ ግራ ደግሞ የመጥፎ እድል ምሳሌ ተደርጐ የሚታመን በመሆኑ እጥበቱን ከቀኝ በኩል የመጀመር ድርጊት ሟች በዚያኛው ዓለም መልካም ነገር እንዲገጥመውና ነፍሱ የጀነት እንድትሆን ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

**አስከሬን መገነዝ፣** አስከሬን ለመገነዝ የከፈን ጨርቅ፣ ማግ፣ ጥጥ፣ ቀጭኔና ሽቶ ያስፈልጋሉ። የከፈን ጨርቅ አስከሬኑ የሚለብሰው ልብስ ሲሆን ሟች በህይወት ዘመኑ ይጠቀምበት ከነበረው ከጥጥ ፈትል የተሰራ ልብስ መካከል የሚመረጥ ነው (20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

የሴቶች ከፈን በቁጥር አምስት ሲሆኑ እነዚህም ጉፍታ፣ ሽርጥ፣ ጥልቆሽ እና ሁለት ነጠላ ጋቢዎች ናቸው። ጉፍታ ጭንቅላት የሚሸፈንበት ሻሽ ሲሆን ሽርጥ ከወገብ በታች የሚለበስ ጨርቅ ነው። ጥልቆሽ የሚባለው የአርጐባ ሴቶች ባህላዊ ቀሚስ ነው። ቀሚሱ ተጠልፎ የሚለበስ ሲሆን ለከፈን የሚሆነው ግን ጥልፍ ያልተጠለፈበት ቀሚስ ነው። ሟች ካሏት ቀሚሶች ውስጥ ያልተጠለፈና ምናልባትም ስሞት ለከፈኔ ይሆናል በማለት ያስቀመጠችው ካለ ይመረጣል፤ ነገር ግን ሁሉም ባለ ጥልፍ ከሆኑ ወይም ያላት አንዱ ባለ ጥልፍ ከሆነ ጥልፉ ሙሉ በሙሉ ተተርትሮ ለከፈንነት ይውላል። ለሁለት የተነጠለው ጋቢ በቁጥር እንደ ሁለት የሚቆጠር ሲሆን መካከሉ ይሰፋና የአስከሬን መጠቅለያ እንዲሆን ይዘጋጃል (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 19/5/2013 ገቀ፣ ቃመ)። ጥልፍ መተርተሩ ማጌጥ ዓለማዊ ብቻ በመሆኑ ለሙታን የሚፈለግ አለመሆኑንና ሞት ከሚጌጥበት ዓለም የስጋዊ መገለጫ የሆነ ጌጥ ወደማያስፈልግበት ዓለም የሚደረግ ሽግግር መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

የወንድ ከፈን በቁጥር ሶስት ሲሆኑ እነዚህም ሁለት ነጠላ ጋቢና አንድ ሽርጥ ናቸው። የወንድ የከፈን ጨርቅ ሁለት ነው እና ሶስት ነው የሚል ሀሳብ ከመረጃ ሰጪዎች ቀርቦ ብዥታ ተፈጥሮ የነበረ ቢሆንም ጉዳዩ በቡድን ተኮር ውይይት ላይ ቀርቦ የወንድ ከፈን ሶስት መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል (30/2/2013፣ ጋቀ፣ ቡተው[19])። አቶ መሐመድ አቡበከር የሴት ከፈን አምስት፣ የወንዱ ደግሞ ሶስት ብቻ የሆነበትን ምክንያት "ሴት በቁሟም ከወንድ በተለይ ፀጉሯንና ሌላ አካሏን ትሸፍናለች። ጭማሪውም ይኸው ነው። አንደኛው ጉፍታው ነው። ሁለተኛው ጥልቆው ነው። ወንድ ግን ሽረጥ

[19] ቡድን ተኮር ውይይት

አድርጐ ቢሄድም ብዙ ችግር የለበትም በቁሙም ቢሆን። ስለዚህ ሴቷ መሸፈኗ ውበቷ ስለሆነ ጨመር ይላል" በማለት አስረድተዋል (6/2/2013፣ *ጋቀ*፣ *ቃመ*)።

ከጥጥ ተፈትሎ የሚዘጋጅ ማግ አስከሬን ተከፍኖ ካለቀ በኋላ አምስት ቦታ ላይ ለመቋጠር የሚጠቀሙበት ነው። ብዙ አርጐባዎች በቤታቸው ውስጥ ለአስከሬን መገነዣ ብለው ማግ ያስቀምጣሉ። ነገር ግን በአጋጣሚ ማግ ካልተገኘ ከመከፈኛው ጨርቅ ተቀርጦ እንደ ማግ መጠቀም እንደሚቻል ወ/ሮ ሞሚና መሐመድ ገልፀዋል (19/4/2013፣ ጨቀ[20]፣ *ቃመ*)። ቀጭኔ መልካም መዓዛ ያለው ቅጠል ሲሆን ደርቆና ታሽቶ ሲደቅ በተነደፈ ጥጥ ላይ እየተነሰነሰ በአስከሬን የተለያዩ ቦታዎች ላይ ይደረጋል። አስከሬኑ ተከፍኖ ካበቃ በኋላ ሽቶ የሚርከፈከፍበት በመሆኑ ሽቶም ያስፈልጋል።

አስከሬን የሚገነዘው ድንክ አልጋ ላይ በመሆኑ አልጋው ላይ ቅጠል ይረበረብና እዚያ ላይ የተዘጋጀው ማግ እጥፍ እጥፍ እየተደረገና ለማሰር በሚያስችል ቁመት እየተቆረጠ አስከሬኑን ጭንቅላት፣ ትከሻ፣ ወገብ፣ ጉልበትና ቁርጭምጭሚት ላይ ለማሰር በሚያስችል መልኩ አምስት ቦታ ላይ ይጣላል። ከዚያ በላይ ነጠላ ጋቢው በስተግራ ያለው ተረፍ እንዲል ተደርጐ ይዘረጋል (20/2/2013፣ *ጋቀ*፣ ም)።

አስከሬኑ ታጥቦ እንዳበቃ ሽርጡ ይሸረጥበትና አስከሬኑ የተሸፈነበት ጨርቅ ይነሳል። ከዚያ በኋላ አስከሬኑን ከታጠበበት ጣውላ ላይ በማንሳት አልጋው ላይ በጀርባው ይደረግና የመገነዝ ስራው ይቀጥላል። ሟቿ ሴት ከሆነች ከሽርጡ በኋላ ጥልቆሹ ይጠለቅና እስከ እግር ድረስ ይለበሳል፤ ጉፍታው ይለበስና ጠበቅ ተደርጐ አገጭ ስር በመርፌ ተሰፍቶ ይያያዛል (20/2/2013፣ *ጋቀ*፣ ም)። ሟቹ ወንድ ከሆነ ሽርጥ ብቻ ይሸረጥለታል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ *ጋቀ*፣ *ቃመ*)። ከዚያ በኋላ አስከሬኑ በነጠላ ጋቢው ከመጠቅለሉ በፊት ንድፍ ጥጥ እየተቦጨቀና ቀጭኔ እየተነሰነሰበት እርጥበት ሊኖር ይችላል ተብሎ በሚታሰብበት የሰውነት ክፍል ላይ ሁሉ ይደረጋል። በመሆኑም ሟቿ ሴት ከሆነች ሀያ አራት ቦታ ላይ ማለትም በእጅና በእግር ጣቶች መካከል ላይ፣ በአፍንጫና በጆሮ ቀዳዳዎች ላይ፣ ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ የሚቦጨቀውን ንድፍ ጥጥ መጠን ከፍ በማድረግና አሁንም ቀጭኔ በመነስነስ በአስከሬኑ ፊት ላይ ሙሉ በሙሉ፣ በብብትና በብብት ውስጥና በብልት ላይ ይደረጋል (20/2/2013፣ *ጋቀ*፣ ም)። ሟቹ ወንድ ከሆነም በብልት ላይ ከሚደረገው ጥጥ ውጭ በተመሳሳይ መንገድ በሁሉም ቦታ ላይ ጥጥ ይደረጋል (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ *ጋቀ*፣ *ቃመ*)። ከዚያ በኋላ ሽቶ ይርከፈከፍና ነጠላ ጋቢው መጀመሪያ ከቀኝ በኩል፣ በመቀጠል ከግራ በኩል መለስ መለስ ተደርጐ አስከሬኑ ይሸፈንበታል። ከዚያ በኋላ ነጠላ ጋቢው ከእግር ተረፍ ተደርጐ በደንብ እየተለበሰና ከስር በተዘረጋው ማግ እየታሰረ ጭንቅላት ጋር ሲደርስ ነጠላ ጋቢው ከጭንቅላት በላይ በደንብ ተለብሶና ተጠቅልሎ በማጉ ይታሰራል። ከዚያ በኋላ እንደገና ሽቶ ይርከፈከፍና በነጠላ ይሸፈናል (20/2/2013፣ *ጋቀ*፣ ም)።

---

[20] ጨኖ ቀበሌ

መልካም መዓዛ ያለውን ቀጭኔ በጥጥ እያደረጉ በተለያዩ የአስከሬኑ ክፍሎች ላይ ማድረግና ሽቶ ማርከፍከፍ ለአስከሬኑ ጥሩ መዓዛ ለመስጠት ዓላማ ከመደረጉ ባሻገር ትዕምርታዊነት ያለው ድርጊትም ነው። አርጐባዎች ከጀነት መገለጫዎች መካከል አንዱ መልካም መዓዛ እንደሆነ የሚያምኑ በመሆኑ ይህን ማድረጋቸው የሟች ነፍስ የጀነት እንዲሆን በመመኘት ለማምሰልም ነው።

በየትኛውም ዓይነት አሟሟት የሞተ እና በየትኛውም ማኅበራዊ ደረጃና እድሜ ላይ ያለ ሰው ሲሞት የአስከሬን አጥበትና አገናነዙ ተመሳሳይ ነው (አቶ መሐመድ አቡበከር፣ 6/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬኑን የሚያጥቡና የሚገንዙ ወንዶች ሲሆኑ ሴት ከሆነች ደግሞ አጥበው የሚገንዙ ሴቶች ናቸው። ነገር ግን ወንድ ሰው ሲሞት ሴቶች ንድፍ ጥጥና ቀጭኔ በማዘጋጀት ወንዶቹን ሊረዷቸው ይችላሉ (20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

### 5.2.7. የአለቃቀስ ሥነ ስርዓት፣ ለቅሶ የመድረስና የመረዳዳት ልማድ

በአርጐባዎች ዘንድ ሀዘንን የማጥበቅና ምርር ብሎ የማልቀስ ልማድ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ግን የሀይማኖት አባቶች እየከለከሉ ይህ አይነት የለቅሶ ሁኔታ እየቀረ መጥቷል። በመሆኑም ሰዉ ቁጭ ብሎ እያለቀሰ ሀዘኑን ይገልፃል እንጂ ምርር ብሎ ማልቀስ፣ መጮህ፣ ማርገድ፣ መዝለል፣ ደረት መምታት፣ ራስን መጉዳት፣ እየተንጐራደዱ፣ ግጥም እየገጠሙና ዜማ እየቀረጡ ማልቀስ፣ ሟችን በግጥም ማወደስ፣ የተለየ መልበስ፣ ወዘተ በአርጐባ የሚታሰብ አይደለም። ሀዘኑ አሸንፎት ምርር ብሎ የሚያለቅስ ሰውም ተው ተብሎ ይገሰፃል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

ቁጭ ተብሎ ሲለቀስ ሟችን እያነሱና በባህርዩና በመልኩ እያወደሱ ማልቀስ የተለመደ ነው። ሟች በህይወት በነበረች ጊዜ ጐረቤቶቿን የምትጠቀም፣ የምትረዳ፣ የምታበላና የምታጠጣ ከሆነች ይህንኑ ደግነቷን እያነሱ ያለቅሳሉ። ሟች ጐበዝ ገበሬ ከነበረ ይኸው ጉብዝናው እየተነሳና እየተሞካሸ ይለቀሳል። ሟች ቆንጆ ከነበረች ወይም መልከ መልካም ከነበረ ቁንጅናና ቁመና እየተነሳ፤ የኔ ብርሌ፣ የኔ ቆንጆ እየተባለ ይለቀሳል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

ሞት ሲከሰት የሚለቀሰው በዋናነት ሁለት ጊዜ ሲሆን አንደኛው ነፍስ ስትወጣ፤ ሁለተኛው ደግሞ አስከሬን ከቤት ሲወጣ ነው። ሞት ሲከሰት በአካባቢው ያሉ የቤተሰብ አባላትና ዘመዶች፤ ምናልባትም ጐረቤቶች ያለቅሳሉ። አስከሬን ከቤት ሲወጣ ደግሞ ሴቶች ቆመው እያለቀሱ ይሸኛሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)። በአንድነት ተሰብስቦ ማልቀስ መበርታትን፣ ሥነ ልቡናዊ እፎይታን፣ እረፍትን ያስገኛል። ሀዘንተኞች የሚደርስባቸውን ሀዘንና እምቅ ስሜት በማቅለል ሥነ ልቡናዊ ፋይዳ ያስገኛል።

በእስልምና አስተምህሮ መሰረት ሰዎች በሚሰበሰቡባቸው ሥነ ስርዓቶች ሁሉ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ተደባልቀው አይቀመጡም (The Quran 33:53)። በመሆኑም በለቅሶ ሥነ ስርዓት ጊዜም ሴትና ወንድ ለቅሶ ደራሾች የሚቀመጡት ለየብቻ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች በሀዘኑ ቤት ውስጥና በደጅ በየጥላው ስር ሲሆኑ ወንዶች ደግሞ በዳስ ውስጥ ይሆናሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

በአርጐባዎች ዘንድ ለቅሶ አለመድረስ ወዳጅነትንና አንድነትን የሚያሳጣና ቂም የሚያያይዝ ከባድ ጉዳይ ነው። ዘመድና ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት እየተመላለሱ ከማጽናናት በተጨማሪ ለሀዘንተኞች የጉልበት፣ የዓይነትና የገንዘብ እገዛ ያደርጋሉ (ወ/ሮ ሀይሀሊማ ሱለይማን፣ 21/5/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

በአርጐባዎች ዘንድ ያለው ጠንካራ ለቅሶ የመድረስ ልማድ ተግባቦታዊ ፋይዳ አለው። ሰዎች በለቅሶ ቤት መገኘታቸውና በሚከወኑ ሥነ ስርዓቶች ላይ መሳተፋቸው ለሀዘንተኞች ያላቸውን ቀረቤታና አጋርነት ማሳየታቸው ነው። ሰዎች ወደ ለቅሶ ቤት በመሄድ ከሀዘንተኞች ጋር አብረው ሲሆኑ፣ አብረው ሲያለቅሱ፣ ቤቶቻቸውን ትተው ከሀዘንተኞች ጋር ሲውሉና ሲያድሩ፣ ሀዘንተኞችን ሲረዱ፣ የተፈጠሩ ችግሮችን ሲቀርፉ፣ ሀዘንተኞች ቁጭ ብለው ጐረቤቶች የቤቱን ስራ ሲያከናውኑ፣ ምግብ ከየቤታቸው በመውሰድ መሸኛና ማምሻ ሲያዘጋጁ፣ ሰው ሲያስተናግዱ፣ የመቃብር ጉድጓድ ሲቆፍሩ፣ አስከሬን አጥበው ሲገንዙ፣ አስከሬን ወስደው ሲቀብሩ፣ ወዘተ ሰዎቹ ሀዘንን እየተጋሩ መሆኑን እየገለፁ፣ ለሀዘንተኞቹ ያላቸውን ቅርበት፣ ፍቅርና አጋርነት እያሳዩ ነው። በተጨማሪም ሰዎች ከሀዘንተኞች ጋር ባላቸው ግለሰባዊ ግንኙነት ምክንያት በለቅሶ ሥነ ስርዓቶች ላይ በመሳተፍ ማኅበራዊ አንድነታቸውን ያስጠብቃሉ። ሰዎች ባለመነጣጠላቸውና የለቅሶ ሥነ ስርዓትን በመሰለው አጋጣሚ በመገኘታቸው ቅርበታቸውን ያስመሰክራሉ፤ አንድነታቸውን ያጠናክራሉ። ለቅሶ ደራሾች ለሀዘንተኞች የሚያደርጉት የገንዘብና የዓይነት ስጦታም ለሀዘንተኞች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳን ያስገኛል።

### 5.2.8. በቀብሩ ቀን በሀዘኑ ቤት የሚከወን ሥነ ስርዓት

በቀብሩ ቀን የቀብር ሥነ ስርዓቱ ከመከናወኑ በፊት በሀዘኑ ቤት የሚገኙት በብዛት ሴቶች ሲሆኑ ብዙ ወንድ በዚያ ሰዓት እዚያ አይገኝም። ምግብና መጠጥ የሚያዘጋጁም ሆነ ለቅሶ ለመድረስ የመጡ ሴቶች የሚቆዩት በሀዘኑ ቤት ነው። ንፍሮ የሚቀቅሉና ሌሎች ስራዎችን የሚያከናውኑ እንዲሁም ሟቹ ወንድ ከሆነ አስከሬን የሚገንዙ ጥቂት ወንዶች ቢኖሩም ብዙዎቹ ወንዶች የቀብር ጉድጓድ ቁፋሮ ለማከናወን በመቃብር ስፍራው ይቆያሉ፤ ሌሎች ወንዶችም በተለይ ሀይማኖታዊ እውቀት ያላቸው ሰለዋት ጂናዛ[21] በሚደረግበት መስጊድ ወይም የመቃብር ስፍራ በመሆን አስከሬኑን ይጠብቃሉ (አቶ አቡበከር መሐመድ ኑር፣ 28/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

በሀዘኑ ቤት የምግብና መጠጥ ስራው እየተከናወነ ከሩቅም ይሁን ከቅርብ የመጡ የሟች ዘመዶችና ወዳጆች እንዲሁም ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት ይሰበሰባሉ። የምግብ ዝግጅቱ እንዳበቃ ምግብ ይቀርብና ከሩቅ የመጡ እንግዶችን በማስቀደም ለቅሶ ደራሾች በሙሉ ይስተናገዳሉ። ለመቃብር ቆፋሪዎች፣ በመስጊድ ሰለዋት ጂናዛ ለሚሰግዱ የሀይማኖት መምህርና ደረሶች እንጀራ ተፈትፍቶ ይላካል። በዚያ ቀን በተጣለው ዳስ ውስጥ ወንዶችና ከሩቅ ቦታ የመጡ ሴቶች ይስተናገዱበታል። ከቀብር በኋላ ግን በዳሱ ውስጥ የሚያርፉትና የሚስተናገዱት ወንዶች ብቻ ይሆናሉ። ወንዶችን የሚያስተናግዱ

[21] ለሙት የሚደረግ ስግደት

ወንዶች ሲሆኑ ሴቶችን የሚያስተናግዱ ደግሞ ሴቶች ናቸው (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

### 5.2.9. ለአስከሬን ከቤት ሲወጣ የሚከወን ሥነ ስርዓት

አስከሬን ወደ መስጊድ ወይም/እና ወደ ቀብር ስፍራ የሚወሰደው አስከሬኑን እስከተገነዘበት አልጋ በመሸከም ሲሆን እድሜ ሳይለይ አቅም ያላቸው ወንዶች በሙሉ እየተጋገዙ አስከሬን ይሸከማሉ። በጉዞው ላይ አስከሬን ያልተሸከሙ ሰዎች ቀድመው አስከሬኑን ተሸክመው የሚጓዙ ሰዎች ይከተላሉ። ቀባሪዎች የሚቀምሱት ንፍሮና የቦላ ስጋም ይላካል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

አስከሬን ከቤት ሲወጣ በሀዘኑ ቤት የተሰበሰቡ ሴቶች እያለቀሱ አስከሬን ይሸኛሉ (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)። ሴቶች አስከሬን ይሸኛሉ እንጂ ሀይማኖታዊ በሆነ ምክንያት (Ismaiel num. 1278) አስከሬን ለመቅበር አይሄዱም።

አስከሬን ከቤት ከወጣ በኋላ አብዛኛዎቹ ለቅሶ ለመድረስ በሀዘኑ ቤት የተገኙ ሴቶች ሀዘንተኞችን ተሰናብተው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። የሚሰናበቱት ሴት ሀዘንተኞችን ሲሆን ወደ ሀዘንተኞች ቀርበውና የሀዘንተኞቹን እጅ ይዘው ሟች አዋቂ ሰው ከሆነ/ች "እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ[22]፤ ሟቹንም/ሟቿንም አላህ ይማረው/ይማራት" በማለት፤ ሟች ህፃን ከሆነ/ች ደግሞ "እናንተንም አላህ ይሶብራችሁ፤ እሱንም/እሷንም ሸፍዓ[23] ያድርገው/ያድርጋት" በማለት ነው። ህፃን የጀነት ነው ተብሎ ስለሚታመን ይማረው አይባልም። ከዚያ በኋላ ለቅሶ ደራሾች እንደ አቅምና ከሀዘንተኞች ጋር እንዳላቸው ቀረቤታ መጠኑ ሊለያይ የሚችል ገንዘብ ለሀዘንተኞች በማስጨበጥ ይሰጧቸዋል (17/11/2012 እና 20/2/2013፣ ጋቀ፣ ም)።

አስከሬን ከቤት ከወጣ በኋላ ሰለዋት ጀናዛ በመስጊድ ቅጥር ግቢ ወይም በቀብር ስፍራ ይደረጋል። ሰለዋቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሰጋጆች የሟች ቤተሰብ አባልን ወይም አባላትን፣ ሟች ቤተሰብ ከሌለው ደግሞ ቀረብ የሚለውን ዘመድ ከብበው በመቀመጥ ከቁርዓን ውስጥ ሀዘንተኛው እንዲጽናና እና ሟችም በፈጣሪ ዘንድ ምህረት እንዲያገኝ የሚለመንበት ፋቲሃ አንቀጽ ይቀራል፤ ሀዘንተኛው ቆሞ "አሜን" በማለት ይቀበላል (አቶ አቡበከር መሐመድ ኑር፣ 28/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

### 5.2.10. የቀብር ሥነ ስርዓት

የቀብር ሥነ ስርዓት በተቻለ መጠን ቶሎ እንዲከናወን ይፈለጋል። ነገር ግን የቤተሰብ አባል ወይም ዘመድ ይድረስ ተብሎ መጠበቁ እና የቀብር ጉድጓድ ቆፍሮ ለማዘጋጀት ረዘም ያለ ሰዓት የሚወስድ

---

[22] ሰብር/መሶበር መታገስ፣ መበርታት

[23] መማለድ/ አማላጅ

መሆኑ የቀብር ሰዓትን የሚያራዝሙ ምክንያቶች ናቸው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

የቀብሩ ሥነ ስርዓት ሰለዋት ጀናዛ የተደረገው በመስጊድ ከሆነ ሰለዋቱ ሲያልቅ ቀባሪዎች አስከሬኑን ይዘው ወደ ቀብር ስፍራ በመሄድ፤ ሰለዋቱ የተደረገው በቀብሩ ስፍራ ከሆነ ሰለዋቱ እንዳበቃ ሊከናወን ይችላል። በቀብር ስፍራው የቀብሩ ጉድጓድ ተስተካክሎ አልቆ ከሆነ የቀብር ሥነ ስርዓቱን ወዲያው ማከናወን የሚቻል ሲሆን ጥቂት ስራዎች ከቀሩ አስከሬኑን በጥላ ስር በማድረግ ይጠበቃል፤ ስራው ሲጠናቀቅ የቀብር ሥነ ስርዓቱ ይከወናል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

አስከሬን የሚቀበረው በቀኝ ጐኑ ፊቱ ወደ ሰሜን አቅጣጫ፣ ጭንቅላቱ ወደ ምስራቅና እግሩ ወደ ምዕራብ ተደርጐ፤ አስከሬኑ በጀርባው እንዳይገለበጥ እግሩ በመጠኑ አጠፍ ተደርጐና አስከሬኑ የሚሸፈንበት ነጠላ ጋቢ በፊቱ በኩል ገለጥ ተደርጐ ፊቱ በግማሽ አፈር እንዲነካው መሬቱ ላይ ተደርጐ ነው (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። በእስልምና ሀይማኖት ስግደት፣ ዝኪርና ሌላውም ሀይማኖታዊ ሥነ ስርዓት የሚደረገው ፊትን ወደ ሰሜን አቅጣጫ በማድረግ በመሆኑ (The Quran 2:144) እዚህም የአስከሬን ፊትን ወደ ሰሜን አቅጣጫ አድርጐ መቅበሩ ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ድርጊት ነው።

በመሆኑም ቀባሪዎች አስከሬኑን በመሸከም በቀብር ጉድጓዱ ውስጥ ላሉ ቀባሪዎች ሲያቀብሏቸው ጉድጓዱ ውስጥ ያሉ ቀባሪዎች አስከሬኑን ተቀብለው ከላይ በተገለፀው መልኩ አስተካክለው አስከሬኑን በለኽዱ ውስጥ ያስተኛሉ። ቀባሪዎቹ አስከሬኑን በአግባቡ ማስተኛታቸውን ሲገልፁ እነርሱን በመከተል ቀባሪዎች ቁርዓን መቅራት ይጀምራሉ (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

ሟች ከተቀበረ ጊዜ ጀምሮ ለሰባት ቀናት ያህል የመጠየቂያው ጊዜ ነው። መላዒካዎች በመቃብር እየቀረቡ ጌታው ማን እንደሆነና ሌሎችም ጥያቄዎችን ያቀርቡለታል፣ እርሱም ለሚቀርቡለት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል። ሰባቱ ቀን ሟች በጥያቄ የሚያዝበት የጭንቅና የፍርሀት ጊዜ እንደሆነ ይታመናል። በመሆኑም ቀብር እንደተከናወነ ሟች በመቃብሩ ውስጥ ሆኖ እንደሚሰማ ስለሚታመን ለሚመጣበት ጥያቄ መስጠት ያለበት መልስ ቁርዓን እየተቀራ ይነገረዋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

ቁርዓኑ እየተቀራ ለኽዱ በድንጋይ ተዘግቶ፤ ዙሪያውና በመሀል በመሀል ክፍተት ያለበት ቦታ በትንንሽ ድንጋዮች እየተሞላ በጭቃ ይመረግና አስከሬኑን ያስተኙና ድንጋዩን የዘጉ ሰዎች ከጉድጓዱ ወጥተው አፈር ተመልሶ የፊት ለፊቱ ጉድጓድ ይሞላል። ለኽዱን የመዝጋትና አፈር የመመለስ ስራው በህብረት የሚከናወን ሲሆን ቀባሪዎቹ ስራውን እየሰሩ በተመሳሳይ ሰዓት ቁርዓኑንም እየቀሩ በእኩል ሰዓት ያጠናቅቃሉ። ከዚያ በኋላ በመቃብሩ ላይ ውሃ ተርከፍክፎ እርጥብ ቅጠል ይጐዘጐዛል፤ ሀይማኖታዊ በሆነ ምክንያት የቀብር ቦታን መገንባት ክልክል በመሆኑ ለምልክት ያህል ድንጋይ ይቀመጣል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። በብሔረሰቡ ዘንድ ሞት የመጨረሻ እንዳልሆነና ከሞት በኋላም ህይወት ያለ መሆኑ፤ ከሞት በኋላ ባለው ዓለም ደግሞ ጀነት ቀዝቃዛ፣ ወንዞችና

ጅረቶች የበዙበት፣ እርጥብ ቅጠሎች ባሏቸው ዛፎች የተሞላ እንደሆነ ይታመናል። ቀዝቃዛ ውሃና እርጥብ ቅጠል የህይወትና የልምላሜ ምልክቶችም ናቸው። በመሆኑም መቃብር ላይ ውሃ ማርከፍከፍና እርጥብ ቅጠል መጐዝጐዝ ሟች ከሞት በኋላ ያለ ህይወቱ ህይወት ካለው ከጀነት እንዲሆን መመኛና ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊቶች ናቸው።

የቀብር ሥነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ በአብዛኛው ሩቅ ከሆነ አካባቢ የመጡና የማያድሩ ቀባሪዎች ሀዘንተኞችን ተሰናብተው፤ በሌላ ቀን የማይመለሱ ከሆነም የገንዘብ ስጦታ ሰጥተው በዚያው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ። ቀባሪዎች ሊሄዱ ሲሉ የተላከውን ንፍሮና ቦላ የሚያድሉ ሁለት ሁለት ሰዎች በመሆን ቀባሪዎች በሚሄዱባቸው መንገዶችና አቅጣጫዎች ሁሉ በመቆም ለቀባሪዎች ከንፍሮውና ከቦላ ስጋው በእጅ በእጃቸው ያድሏቸዋል (አቶ አሕመድ ሲራጅ፣ 28/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። ጐረቤትና ከሩቅ ቦታ መጥቶ የሚያድር ወይም ሀዘንተኞችን አጅቦ ቤት አስገብቶ ለመሄድ ያሰበ ወዳጅ ዘመድ የሆነ ቀባሪ ወደ ሀዘኑ ቤት ይመለሳል። ቀባሪዎቹ እንደተመለሱ በሀዘኑ ቤት ሲደርሱ ውሀ ይዘው የሚጠብቋቸው ሰዎች እያስታጠቧቸው ሁሉም እጃቸውን እየታጠቡ ወደ ዳሱ ይገባሉ። ከዚያ በኋላ ንፍሮ በትሪ እየተደረገ በቡድን በቡድን ይቀርብላቸዋል፤ ቡናና ሻይም ይቀርባል። ከዚያ በኋላ ሰለዋት ይጀመራል። የሰለዋት መጽሐፍ ባለ ብዙ ገጽና በአንድ ጊዜ ቁጭታ የማያልቅ በመሆኑ በቀብሩ ቀን አንድ ምዕራፍ ብቻ ያልቅና ሰዎች ደክሟቸው ውለው ሊሆን ይችላል ተብሎ በይደር ይቀመጣል። ከዚያ በኋላ ምሽት ድረስ ሀዘንተኞችን ሲያጽናኑና ሲጫወቱ ይቆያሉ። ከሩቅ ቦታ የመጡ ለቅሶ ደራሾች ሀዘንተኞችን አስተዛዝነው ሲሄዱ ተሰናብተው የሚሄዱ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ወንድ ለቅሶ ደራሾች ወንድ ሀዘንተኞችን፣ ሴት ለቅሶ ደራሾች ደግሞ ሴት ሀዘንተኞችን ይሰናበታሉ። የአካባቢ ሰው ግን በጉርብትናው መሰረት ተመላልሶ ሀዘንተኞችን ስለሚያጽናና አይሰናበትም (አቶ ኢብራሂም መሐመድ ሰዒድ፣ 27/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)። እጅን በውሀ መታጠብ ከንጽህና ዓላማ ባሻገር የሆነ ትርጉምን የያዘ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። ውሀ ህይወትን፣ መንፃትን፣ ተስፋንና መሻገርን ይወክላል። ከቀብር የሚመለሱ ሰዎች እጃቸውን መታጠባቸው ከገጠማቸው ሞት ባሻገር ህይወትን መሻታቸውን ወይም መናፈቃቸውን፣ ከደረሰው ሀዘን ወደ ህይወት መሻገር መፈለጋቸውንና መመኘታቸውን፣ ከደረሰው የሀዘን ስሜት መውጣትንና ህይወትን፣ ተስፋን መመኘታቸውን ይገልፃል።

### 5.2.11. የሀፈሻ ሥነ ስርዓት

ከቀብሩ ቀን በኋላ ያሉት ስድስት ቀናት የለቅሶ ቀናት ናቸው። የሀፈሻ ሥነ ስርዓት በእነዚህ ቀናት ማታ ማታ ጐረቤቶች ምግብ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት በመሄድ ሀዘንተኞችን የሚያስተዛዝኑበት ሥነ ስርዓት ነው። በሀዘኑ ጊዜ ሀዘንተኞች፣ ጐረቤቶችና ከሩቅ የሚመጡ ለቅሶ ደራሾች የሚስተናገዱት ጐረቤቶች ባመጡት ምግብ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ምንም የሚዘጋጅ ነገር አይኖርም። ጐረቤቶች ይዘው የሚሄዱት ምግብ እንደየአቅማቸው ሁለትም ሶስትም እንጀራ ከወጥ ጋር፣ ቡና፣ ሻይና ቆሎ ነው። እንጀራና ወጡ የሚወሰደው ለየብቻ ሆኖ ሲሆን በሀዘኑ ቤት ከሁሉም ቤት የሚሄደው እንጀራና ወጥ በአንድ ላይ ተቀይጦ በየመመገቢያ ሰዓት ከዚያ እየተቀነሰ ይቀርባል (3/10/2012፣ ገቀ፣ ም) (አቶ ኢብራሂም መሐመድ ሰዒድ፣ 27/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)።

ለለቅሶ ቤቱ ከሚመጡ የበሰሉ ምግቦች በተጨማሪ ሰዎች ለሀዘንተኞች እንዳላቸው ቅርበትና ወዳጅነት ማሽላ ወይም ጤፍ ጭነው፣ ፍየል ስበው፣ ሽሮና በርበሬ አስፈጭተው ይዘው ሊሄዱ ይችላሉ። ይህ በሚሆን ጊዜ በሀዘኑ ቤት እህሉ ተፈጭቶ ይጋገራል፣ ፍየሉም ታርዶ ወጥ ይሰራበታል። የምግብ ማዘጋጀቱን ስራም ጐረቤት የሆኑ ሴቶች ይወጡታል (3/10/2012፣ ገቀ፣ ም)። በእነዚህ ቀናት ሴት ሀዘንተኞች በተነጠፈ መዋስ ላይ ቁጭ በማለት ሴት ለቅሶ ደራሾችን፤ ወንድ ሀዘንተኞች ደግሞ በተጣለው ዳስ ውስጥ በተጐዘጐዘ ቅጠል ላይ ቁጭ ብለው ወንድ ለቅሶ ደራሾችን ይቀበላሉ (አቶ ኢብራሂም መሐመድ ሰዒድ፣ 27/3/2013፣ ላመቀ፣ ቃመ)።

ይህንን የሽግግር ጊዜም ከሟችና ከሟች ቤተሰብ አንፃር መመልከት ይቻላል። ከሟች አንፃር ይህ ጊዜ ሟች ከገሀዱ ዓለም የተነጠለበት ነገር ግን ነፍሱ ወደ ዘላቂው የሙታን ዓለም ያልተቀላቀለችበት፣ በመቃብር ሆኖ ጥያቄ የሚጠየቅበት፣ የሚጨነቅበት፣ የነፍሱ መዳረሻ ገና ያልተለየበት ጊዜ ነው። ከሟች ቤተሰብ አንፃር ሲታይም ይህ ጊዜ የሟች ቤተሰብ አባላት ሀዘንተኞች በመሆናቸው ቀደም ሲል ከነበራቸው የቀን ተቀን እንቅስቃሴ የተነጠሉበት ጊዜ ነው። በዚህ ጊዜ ቤተሰቡ በተከሰተው ሀዘን መረበሽና መጨነቅ የሚደርስበት፣ ማኀበራዊ ኑሮውን የማይጀምርበት፣ የቤት ውስጥ ስራዎችን የማያከናውንበትና ከሌላው ቀን በተለየ አብሮ የሚመገበው ጐረቤቶች አዘጋጅተው የሚያመጡለትን ምግብ የሚሆንበት ጊዜ ነው።

## 5.3. መቀላቀል

የመቀላቀል ደረጃ ከቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያሉ የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች የሚከወኑበትን ጊዜ በሙሉ ያጠቃልላል። ቆዳ ማጠፊያ የመጀመሪያው የመታሰቢያ ሥነ ስርዓት ሲሆን የሟች ነፍስ ወደማይታየው ዓለም እንደምትቀላቀል የሚታመንበት፤ ሀዘንተኞችም በመጠኑ ወደቀደመው የቀን ተቀን የህይወት እንቅስቃሴያቸው የሚመለሱበት በመሆኑ የመቀላቀል ደረጃ የሚጀምርበት መነሻ ነው።

የመቀላቀል ጊዜ ዋና መገለጫዎች የሆኑት የመታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች በብሔረሰቡ ዘንድ ባሉ ሞት የመጨረሻ ጉዳይ ሳይሆን አሻጋሪ ነው፤ የሟች ነፍስ ከሞት በኋላ ከገሀዱ ዓለም ተነስታ ወደማይታየው ዓለም ትደርሳለች፤ አንድ ጊዜ ከገሀዱ ዓለም የተለየች ነፍስ ደግሞ መንገዷ እንዲስተካከል፣ ከፈጣሪ ምህረት እንድታገኝና በዚያኛው ዓለም እንድትደላደል የመታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች ተደርገው ሶደቃና ዱዓ ማድረግ ያስፈልጋል የሚሉ እምነቶች መሰረትነት የሚከወኑ ናቸው።

ሶደቃ የሚቀርብ ምግብና መጠጥ ነው። ሶደቃ የሚደረገው የሟች ነፍስ ወደ ወዲያኛው ዓለም የምታደርገውን ጉዞና በዚያ የሚኖራትን ቆይታ ጥሩ ያደርጋል፤ ከፈጣሪ ምህረትን እንድታገኝና የጀነት እንድትሆን ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው። በየጊዜው የሚደረገው ሶደቃም ሟች በህይወት ዘመኑ የሰራውን ሀጢያት እየሸረፈ፣ እየቀነሰ በመሄድ ነፃ ያደርገዋል፤ ምህረት ያስገኝለታል ተብሎ ይታመናል (አቶ መሐመድ ሱአሊ ሱፌማን፣ 4/4/2013፣ ጨቀ፣ ቃመ)። ሶደቃ ማድረግ ለቋሚም ዋጋ እንደሚያስገኝ ይታመናል። ይህን በተመለከተ አቶ አሕመድ ሲራጅ "በመጀመሪያ ሰው ስታበዪ ምንዳ አለሽ ከፈጣሪ። ስታመሰግኝም፣ የፈጣሪን ጥሩነት ስትናገሪም ምንዳ አለው። ዋጋው ለሟች

ይሁን ነው የምንለው። ለሱም ስንል ለእኛም ደግሞ አይቀርም። ለቋሚውም ይመዘገብለታል። ለሟች በማሰባችን ለእኛም አለን'' ብለዋል (28/2/2013፣ *ጋቀ፣ ቃመ*)። በአንፃሩ ለሙታን የሚደረግ ሶደቃና ዱዓ መጓደል በቋሚዎች ላይ ችግር እንደሚያስከትል፤ ሶደቃ ቢጓደል የሟች ነፍስ ወደ ሟች ቤተሰብና ዘመዶች በመመለስ ቋሚን እንደምትረብሽና በአካባቢው ድርቅ ወይም የዝናብ እጥረትን እንደሚያስከትል ይታመናል (ወ/ሮ ሲቲ ፋጡማ መሐመድ፣ 10/2/2013፣ *ጋቀ፣ ቃመ*)። ሶደቃውን የሚቀምሰው ሰው ቁጥር ሲበዛ ሶደቃ በማድረግ የሚገኘው ጥቅምም እንደሚበዛ ይታመናል። ለምሳሌ ከቀብር በኋላ ለቀባሪ የሚሰጠው ቦሎ ስጋ ጥሬ እንዲሆን የተደረገው ወሳጁ ሰው ስጋውን ወደየቤቱ ወስዶና ቀቅሎ ሌሎች የቤተሰብ አባላት ከመረቁ እንዲቀምሱና የሶደቃ ቀማሹ ሰው ቁጥር እንዲበዛ ሲባል ነው። በመሆኑም ሶደቃ ማድረግ የሟች ነፍስ ጥሩ መንገድ እንደምታገኝና ቋሚም ከሞት በፊትም ሆነ ከሞት በኋላ መልካም ነገር እንደሚያገኝ በማመን የሚደረግ ሲሆን የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች ዋና መገለጫ ነው። ከዚህ በታች የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች ክዋኔ ቀርቧል።

### 5.3.1. የቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት

ሞት ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ እስከ ቆዳ ማጠፊያ ቀን ድረስ ያሉ ስድስት ቀናት የለቅሶ ቀናት ሲሆኑ ሀዘንተኞች የእለት ተእለት ስራቸውን የማያከናውኑባቸውና ሀዘንተኞች በመሆናቸው ቁጭ ብለው ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎችን የሚቀበሉባቸው ቀናት ናቸው። የቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት በሰባተኛው ቀን የሚከወን ሲሆን ሀዘንተኞች ዋናውን የለቅሶ ጊዜ ጨርሰው ቀለል ያሉና ከቤት የማያርቋቸውን ስራዎች መስራት የሚጀምሩበት ነው። ሥነ ስርዓቱ ቆዳ ማጠፊያ የተባለው ሴት ሀዘንተኞች ለቅሶ የሚቀመጡት መዋስ በማንጠፍ በመሆኑና ይህ ሥነ ስርዓት የለቅሶ ጊዜ ማብቂያ ሆኖ የተነጠፈው መዋስ ስለሚነሳ ነው (ወ/ሮ አሚናየ መሐመድ፣ 17/3/2013፣ *ላመቀ፣ ቃመ*)።

የቆዳ ማጠፊያ በሚከወንበት እለት ሰዎች ቀኑን ቆጥረውና አስበው ወደ ሀዘኑ ቤት ይሄዳሉ እንጂ ምንም አይነት ጥሪ አይደረግም። በመሆኑም በቆዳ ማጠፊያው ቀን ጠዋት ሴት[24] ዘመዶችና የቅርብ ጐረቤቶች በሀዘኑ ቤት በመገኘት ሴት ሀዘንተኞችን በቃችሁ በማለት ለለቅሶ የተዘረጋው መዋስ ላይ ውሀ አርከፍክፈው በማጠፍ ያነሱታል። መዋሱ ሲታጠፍ እንደ አዲስ ይለቀሳል። ሁሉም ሴቶች እጃቸውንና ፊታቸውን በውሃ ከታጠቡ በኋላ ቡና ተፈልቶ ቁርስ ይቀርብና ዱዓ ተደርጐ ቡናው ይጠጣል (ወ/ሮ አሚናየ መሐመድ፣ 17/3/2013፣ *ላመቀ፣ ቃመ*)።

መዋስ ለቅሶ መኖሩን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ቁስ ነው። በአንድ ቤት ውስጥ የተነጠፈ መዋስ መኖሩ በዚያ ቤት ለቅሶ መኖሩን ገላጭ ነው። መዋስ የመዘርጋትና የማጠፍ ድርጊቶችም ትዕምርታዊ ናቸው። መዋስ መዘርጋት የሞት መከሰትን፣ ሰዎች በአዲስ፣ በትኩስ ለቅሶ ላይ መሆናቸውን፣ ቀጣይ ቀናቶች ሞት በተከሰተበት ቤት የሚታወቅ የለቅሶ ጊዜ መሆኑን የሚያሳይ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። በአንፃሩ መዋስ ማጠፍ የለቅሶ በቃ ማለትን፣ ሞት ካስከተለው የሀዘን ስሜት መውጣትን፣ ተፈጥሮ ከነበረው የሥነ ልቡና ቀውስ ማገገምን፣ መሻገርን፣ መውጣትን የሚወክል ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

---

[24] *መዋስ ላይ የሚቀመጡ ሀዘንተኞች ሴቶች ስለሆኑ የሚያነሱትም ሴቶች ናቸው።*

መዋሱ የሚታጠፈው ጠዋት መሆኑ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። የጠዋት ሰዓት ወፎች መዘመር የሚጀምሩበት፣ አበባዎች የሚፈኩበትና የሌሊት ፍጥረታት ወደ ቦታቸው የሚያፈገፍጉበት ነው። ንጋት አዲስ ቀንን፣ እንደገና መወለድን፣ ተስፋን፣ ብሩህ ነገርንና ለውጥን ይወክላል። በመሆኑም መዋስ የሚታጠፈው በጠዋት መሆኑ በአስጨናቂው ጊዜ ውስጥ እንኳን ሁልጊዜ አዲስ ጅምርና ለውጥ ሊኖር እንደሚችል የሚያሳይ፣ የጨለማ ጊዜን አልፎ ወደ ብርሀን፣ የተከሰተውን ሞትና ያለፉትን የለቅሶ ቀናት ወደ ኋላ ትቶ ወደ አዲስ ቀን ብርሀን መግባትን የሚገልጽ፣ ሞት ካስከተለው የሀዘን ስሜት በመሻገር ብሩህ የወደፊት ተስፋን፣ ህይወትን፣ አዲስ እድሎችን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

መዋሱ የሚታጠፈው ውሀ ተርከፍክፎበት መሆኑና ከተለቀሰም በኋላ በሀዘኑ ቤት የተሰበሰቡ ሴቶች በሙሉ እጃቸውንና ፊታቸውን በውሃ መታጠባቸው ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። ውሀ ህይወትን፣ ተስፋን ይወክላል። ሴቶቹ ውሀ ማርከፍከፋቸውና በውሀ መታጠባቸው የደረሰውን ሀዘን ወደ ኋላ በመተው ተስፋ መናፈቃቸውን፣ ህይወትን መሻታቸውን፣ ውሀን ማብረጃና ማርከሻ ትዕምርታዊ ቁስ በማድረግ ሀዘን እንዲበርድ፣ ሀዘን እንዲበቃና እንዳይደግም መመኘታቸውንና ማምሰላቸውን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

በአርጐባዎች የለቅሶ ሥነ ስርዓት ክዋኔ ተደጋግሞ የሚመጣው ውሃ አርጐባዎች ስለሞትና ህይወት ያላቸውን ግንዛቤ የሚነግር ትዕምርት ነው። ውሃ የህይወት ምልክት ሲሆን አርጐባዎች ውሃን የሚያርከፈክፉበትና የሚታጠቡበት ቦታና ጊዜ ከሞት በኋላ ህይወት አለ ብለው ማመናቸውን የሚገልጽ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። የብሔረሰቡ አባላት ከሞት በኋላ ያለን ህይወት የሚረዱበት መልክ ደግሞ ሁለት ዓይነት ሲሆን አንደኛው ሰማያዊ ህይወት ሲሆን ሁለተኛው ምድራዊ ነው። ሰማያዊውን ህይወት በተመለከተ በመቃብር ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ማርከፍከፋቸው ሞት የመጨረሻ ሳይሆን ከገሀዱ ዓለም ወደማይታየው ዓለም የሚያሻግር ድልድይ ብቻ መሆኑንና ሟች ከሞት በኋላ የሚሄድበት ዓለም መኖሩን፣ በዚያም ህይወት በሞላው ጀነት እንዲኖር መመኘታቸውን ያሳያል። ከለቅሶ ቀናት በኋላ እጅና ፊትን በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ ደግሞ በምድራዊው ዓለም ያሉ የሟች ቤተሰብና ዘመዶች ህይወት ቀጣይ መሆኑን እንዲገነዘቡ፣ ከደረሰባቸው ሀዘን ተሻግረውና ሀዘኑን ወደ ኋላ ትተው ህይወታቸውን እንዲኖሩ ማምሰያ ትዕምርታዊ ድርጊት ነው።

በቆዳ ማጠፊያው ቀን ጠዋት የሟች ወይም የቤተሰቡ ቅርብ የሆኑ ወንዶች ያለማንም አስታዋሽና ያለምንም ጥሪ ተሰብስበው በጠዋት ወደ ቀብሩ ቦታ በመሄድ የመቃብሩን ቦታ ዙሪያውን በድንጋይ ይከባሉ። ካቢዎቹ ከበው ሲጨርሱ ወደ ሀዘኑ ቤት በመምጣት ቁርስ ይበላሉ፤ የሚቀርብላቸው ገበታም የካቢ ገበታ ይባላል። ከዚያ በኋላ እርድ የሚታረድ ከሆነ እርዱን ያከናውናሉ። በዚህ ቀን ሩቅ ቦታ የሚኖሩና ሀዘኑን የደረሱና ያልደረሱም የሟች ዘመዶችና ወዳጆች ቀኑን ቆጥረው ወደ ሀዘኑ ቤት ይሄዳሉ፣ በስራም ያግዛሉ (አቶ ከይላን ያሲን፣ 9/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

ድንጋይ ከመትከልና ዙሪያውን ከመካብ ውጭ በመቃብር ላይ የሚደረግ ሌላ ምልክት አይኖርም፤ ነገር ግን በሀይማኖት በቅተው ለሞቱ አባቶች መቃብሮቻቸው ላይ ቤት ይሰራል። የሚሰራው ቤት ከላይ ጣሪያ ይኑረው እንጂ ግድግዳው በእንጨት ወይም በካብ ይሰራል፤ አምሮና የመኖሪያ ቤት መስሎ አይሰራም። የመቃብር ቤቱ ሄደው ለሚዘይሩ ሰዎች ማረፊያ ይሆናቸዋል (አቶ ከይላን ያሲን፣

9/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)። የመቃብር ቤቱ አምሮ የማይሰራው ማማር የገሀዱ ዓለም መገለጫ እንጂ የሙታን ዓለም መገለጫ አይደለም፤ ለሙታን ዓለም ጌጥ አያስፈልግም በሚል እምነት ምክንያት ነው።

በቆዳ ማጠፊያው ቀን ሴቶች በሀዘኑ ቤት ይሰበሰቡና ምግብና መጠጥ ያዘጋጃሉ። ሞት በተከሰተ ጊዜ የተበጀውና ምግብና መጠጥ ሲዘጋጅበት የነበረው ዳስ ሳይፈርስ የሚቆይ በመሆኑ በሰባቱ ቀን ምግብ ማዘጋጃ ዳስ ማዘጋጀት ሳያስፈልግ ስራው በዚያ ዳስ ስር ይከናወናል። የምሳ ሰዓት ሲሆን ሰዎች ወደ ሀዘኑ ቤት ይሰበሰቡና ወንዶች ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ ተጥሎ በቆየው ዳስ ውስጥ፣ ሴቶች ደግሞ በሀዘኑ ዋና ቤት በመሆን በምግብ ይስተናገዳሉ (26/2/2013፣ ገቀ፣ ም)።

### 5.3.2. የወር መታሰቢያ ሥነ ስርዓት

የወር መታሰቢያ ሥነ ስርዓት ሞት በተከሰተ በወሩ የሚከወን ሥነ ስርዓት ሲሆን ለሀዘንተኞች የለቅሶ ጊዜ ማብቂያ፣ ከለቅሶ መነሻና የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴን መጀመሪያ ነው። ሟቹ ባለትዳር ወንድ ከሆነ ግን የባለቤቱ ለቅሶ መቋጫ የዓግል[25] መፍቻዋ ቀን ነው (አቶ ባባ ከይላን፣ 10/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

ሀዘንተኞች ከቆዳ ማጠፊያው ቀን በኋላ ወዲያው የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴያቸውን አይጀምሩም። በመሆኑም ሀዘንተኞች ከመንደራቸው ርቀው አይሄዱም፣ ገበያ አይሄዱም፣ እህል አያስፈጩም፣ ውሃ አይቀዱም። ይህን መሰሉን ስራ ጐረቤቶቻቸው የሚያከናውኑላቸው ሲሆን እነርሱ ቆይቶ የመጣን ለቅሶ ደራሽ ይቀበላሉ። ከወር መታሰቢያ ሥነ ስርዓት በኋላ ግን ይህ ሁሉ ቀርቶ ሀዘንተኞች ከለቅሶ ተነስተው የእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴያቸውን ይጀምራሉ (አቶ ባባ ከይላን፣ 10/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

የወር መታሰቢያ ሥነ ስርዓት የቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓትን ያህል አይደምቅም፤ ጥሪ ካልተደረገ በስተቀር ብዙ ሰው አይገኝበትም፤ የቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓቱን ያህልም ድግስ አይደገስበትም። አብዛኛውን ጊዜ ለተወሰኑ ሰዎች እንደ አቅም ሁኔታ ምግብ ተዘጋጅቶ ዱዓ ይደረጋል።

### 5.3.3. የዓግል መፍቻ ሥነ ስርዓት

ባለቤቷ የሞተባት ሴት በሀይማኖታዊ ትዕዛዝ ምክንያት ሟቹ ከሞተበት እለት ጀምሮ ለአራት ወር ከአስር ቀን ያህል ቅባትና ሽቶ እንዳትቀባ የምትከለከል ሲሆን (Ismaiel num. 313) ዓግል በክልከላ የምትቆይበት የለቅሶ ጊዜ ነው። ክልከላው ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው ቢሆንም

[25] በሀይማኖታዊ ትዕዛዝ ምክንያት ባለቤቷ የሞተባት ሴት ቅባትና ሽቶ እንዳትቀባ የምትከለከልበት የአራት ወር ከአስር ቀን ጊዜ

ክልከላውን ማንሳትን ተከትሎ የሚከወን ሥነ ስርዓት ግን አለ። ሥነ ስርዓቱ ዓግል መፍቻ የሚባል ሲሆን የሚከወነው በሀይማኖታዊ ትዕዛዝ ምክንያት የተጣለው ክልክል መነሳቱን ለመግለጽና ፈጣሪ ሀዘንን በቃ እንዲል ዱዓ ለማድረግ ነው።

በአርጐባዎች ዘንድ የለቅሶ ጊዜ አንድ ወር፣ ባለቤቷ ለሞተባት ሴት ደግሞ አራት ወር ከአስር ቀን ነው። በዚህ ጊዜ ሀዘንተኛ የሆኑ ሴቶች ከቤታቸው ራቅ ብለው አይሄዱም፤ ውሀ አይቀዱም፣ ወደ ወፍጮ አይሄዱም፣ ቅባት አይቀቡም። የቤት ውስጥ ስራዎቻቸውን ጐረቤቶች ያከናውኑላቸዋል። ነገር ግን ለሟች ባለቤት የዓግል መፍቻ ቀን የለቅሶ ጊዜዋ የሚያበቃበት፣ ከዚያ በኋላ አስተዛዛኝና ለቅሶ ደራሽ ይመጣብኛል የማትልበትና ከሀዘኗ በፊት የምታከናውናቸውን የእለት ተእለት የህይወት እንቅስቃሴዎቿን ማከናወን የምትጀምርበት ቀን ነው። ከዚያ በኋላ ርቃ መሄድ፣ ገበያ መገበያየት፣ ከሰዎች ጋር ያላትን ማኅበራዊ ኑሮ መቀጠል፣ ለአራት ወር ከአስር ቀን ያህል የደረቀ ሰውነቷን በቅባት ማለስለስ፣ ወዘተ ትችላለች (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)። "እከሌ አግሏን ፈትታለች" የምትባለው ከነበረችበት የአራት ወር ከአስር ቀን የሀዘንተኛነት መልክ ወጥታ ከባለቤቷ ሞት በፊት የምታደርጋቸውን የእለት ተእለት የኑሮ እንቅስቃሴዎች ማድረግ ስለምትጀምር ነው።

በዓግል መፍቻው ቀን የሟች ዘመዶች የሆኑ ሴቶች የሟች ሚስት የምትቀባውን ለጋ ቅቤ፣ የምትለብሰውን አዲስ ቀሚስና ሻሽ፣ ድፎ ዳቦና ቆሎ ይዘው ወደ ሀዘኑ ቤት ይመጣሉ። ሟች የሞተበትን ሰዓት ጠብቀው የሟችን ሚስት ገላዋን አጥበው ያመጡትን ቅቤ ለሶስት በመክፈል አንድ እጁን ከራስዋ ጀምረው ገላዋን ሁሉ ቀብተዋት ያመጡትን አዲስ ልብስ ያለብሷታል። በዚህ ጊዜ ይለቀሳል። ለቅሶው ሲያበቃ አዝጋሮና[26] ሽታ[27] ያሞቋትና በተቀባችው ቅቤ ለሰው አይን እንዳትጋለጥ ተብሎ ደበቅ ያለ ቦታ ትቀመጣለች። ከዚያ በኋላ ቡና ተፈልቶ የሟች ዘመዶች ይዘውት የመጡት ዳቦ ቀርቦ ለሟቹና ለዓግል ፈቺዋ ዱዓ ከተደረገ በኋላ ዳቦው ተቆርሶ ከቆሎው ጋር እየተሰጠ ቡናው ይጠጣል። የተረፈውን ሁለት እጅ ቅቤ በማግስቱና በሶስተኛው ቀን ይቀቧትና ከዚያ በኋላ ገላዋን ያጥቧታል (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

የሟችን ሚስት በዚህ መልኩ ቅቤ መቀባት አንድም ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው የቅባት ክልከላ ጊዜው ሲደርስ በመሻር ሀይማኖታዊ ትዕዛዝን መፈፀም ሲሆን አንድም ደግሞ የሟች ሚስትን ለአዲስ ኑሮ ማዘጋጀት ነው። የሟች ዘመዶች የሟችን ሚስት ሰውነቷን በሙሉ ቅቤ መቀባታቸው ግዴታሽን ተወጥተሻል፣ ከታሰርሽበት ተፈትተሻል፣ ነፃ ሰው ነሽ ስለዚህ ከዚህ በኋላ ማግባትና ኑሮሽን መቀጠል ትችያለሽ፣ ቅሬታ የለንም የሚል መልዕክታቸውን የሚያስተላልፉበት ትዕምርታዊ ድርጊት ነው። ቅቤ ከቀቧት በኋላ የሚያለብሷት አዲስ ቀሚስ መሆኑም መጪው ጊዜ ሀዘኗን የምትረሳበት፣ ስለራሷ አዲስ ህይወት የምታስብበት፣ ወደራሷ የምትመለከትበት፣ አዲስ ኑሮን የምትይዝበትና በአዲስ ማንነት የምትገለጽበት እንዲሆንላት ማምሰያ ነው።

[26] ግንዱ ተፈልጦ የብሔረሰቡ ሴቶች ሰውነታቸውንና ልብሳቸውን የሚያሞቁበት ጥሩ መዓዛ ያለው እንጨት ነው።

[27] ጥሩ መዓዛ ያላቸው የእጣን አይነቶች በአንድ ላይ ተወቅጠው የሚዘጋጅና የብሔረሰቡ ሴቶች አዝጋሮ ከሞቁ በኋላ የሚሞቁትና ልብሳቸውንም የሚያሞቁበት ጥሩ መዓዛ ያለው ጭስ ነው።

ሀዘንተኛዋን ቅቤ የመቀባቱ ሥነ ስርዓት ከተከናወነ በኋላ ወንዶች ቁርዓን ይቀራሉ፤ ሴቶች ደግሞ ለዓግል ፊቺዋ እንደ አቅማቸው የገንዘብ ስጦታ በመስጠት "አላህ ይጠግንሽ፤ ነገ ደግሞ ቅቤውን በዓለም የምትቀቢና የምትወጪ አላህ ያድርግሽ" እያሏት ወደየቤታቸው ይሄዳሉ (ወ/ሮ አሚና ዝይን፣ 21/2/2013፣ ጋቀ፣ ቃመ)።

### 5.3.4. ጦም ቆሎ

ጦም ቆሎ በረመዳን ፆም ወር የሚደረግ የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓት ነው። የሥነ ስርዓቱ ክዋኔ ዓላማ በቆሎ ወይም በተገኘው ነገር ሙታንን ማሰብ ሲሆን በፆም ወቅት በመደረጉ ፈጣሪ የሚችን ሀጥያት በብዙ ይሽራል ተብሎ ይታመናል (አቶ መሐመድ ጀማል በሽር፣ 11/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

### 5.3.5. የክረምት መግቢያ ዚያራ

በአርጐባዎች ዘንድ ያልተሰደቀላቸው ሙታን፣ የተከፈተ ወይም የተደረመሰ መቃብርና የተጋለጠ የሰው አጽም መኖር በክረምት ወቅት የዝናብ እጥረት ወይም ከባድ ዝናብ እንዲኖር ያደርጋል ተብሎ ይታመናል። ይህንን ለማስቀረትና ጥሩ የክረምት ወቅት እንዲመጣ የክረምት መግቢያ ዚያራ ይደረጋል። በመሆኑም በሰኔ ወር ላይ ይህን የሚያስተባብሩ ሰዎች በየቤቱ በመሄድ ገንዘብ ይሰበስቡና በተሰበሰበው ገንዘብ ምግብ ተዘጋጅቶ ይሶደቃል፤ ወንዶች በቡድን እየሆኑ በየመቃብሩ ስፍራ ሁሉ እየሄዱ ዚያራ ያደርጋሉ፤ የተከፈተ መቃብር አስሰው ይደፍናሉ፤ የተጋለጠ የሰው አጽም ካለም ሰብስበው ይቀብራሉ (አቶ መሐመድ ጀማል በሽር፣ 11/6/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

### 5.3.6. ዚያራ

ዚያራ በመንፈሳዊ ህይወታቸው የበቁ ሼሆች ከሞቱ በኋላ የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ የሚያደረግላቸው መታሰቢያ ነው። ዚያራን የመከወኑ ዋና ዓላማ እንደሌላው የሙታን መታሰቢያ የሟች ነፍስ ምህረት እንድታገኝ ተማፅኖ ማድረግ ሳይሆን በረከት ለማግኘት፣ ለመማፀንና ስዕለት ለማድረግ፣ ስዕለት ለመክፈል፣ ሟቾችን ለመዘከርና ለማሞገስ ነው (ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ፣ 18/5/2013፣ ገቀ፣ ቃመ)።

ይህ ጊዜ ከሟች አንፃር የሟች ነፍስ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ የምትቀላቀልበት፤ ከሀዘንተኞች አንፃር ደግሞ ሀዘንተኞች ዋናውን የለቅሶ ጊዜ ጨርሰው ቀስ በቀስ ወደቀደመው የህይወት እንቅስቃሴያቸው የሚመለሱበትና ወደ ማኅበረሰቡ ተመልሰው የሚቀላቀሉበት ነው። የዚህ መቀላቀል መሰረት እንደሆኑ የሚታመንባቸው የመታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች በዚህ ጊዜ በዋናነት የሚነሱ ናቸው። እነዚህ መታሰቢያዎች የሟች ነፍስን መንገድና ማረፊያ ያስተካክላሉ፣ ምህረት ያስገኛሉ፣ በተከወኑ ቁጥር የሟችን ሀጢያት እየሸራረፉ የሟች ነፍስን ወደ ጥሩ ማረፊያ ያደርሳሉ በሚል እምነት የሚከወኑና ቋሚም ከሟች ነፍስ ጋር ያለውን ግንኙነት መልክ የሚያስይዝባቸው ናቸው። የሟች ቤተሰብ በቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት ላይ በመሶደቅ፣ የወር መታሰቢያ ሥነ ስርዓትና ጦም ቆሎ በማድረግ የሟች ነፍስ ወደ ማረፊያዋ እንድትሄድ የሚያግዝ ሲሆን ሥነ ስርዓቱን ባለመከወኑ በሟች ነፍስ

ከሚደርስበት ችግርና መረበሽም ይጠበቃል። በእነዚህ የመታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች በጋራ ሆኖ መመገብ መኖሩም የመዋሀድ መገለጫ ነው።

ሀዘንተኞች ከቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት ክዋኔ በኋላ ቀስ በቀስ ቀደም ሲል ወደነበረው ህይወታቸው ይመለሳሉ። የቤት ውስጥ ስራዎቻቸውን ማከናወንና በመጠኑ በማኅበራዊ ህይወት ውስጥ መሳተፍ ይጀምራሉ። ሟች ትዳር ያለው ወንድ ከነበረ ግን የሟች ሚስት የመቀላቀያ ጊዜዋ የሚጀምረው የዓግል መፍቻ ሥነ ስርዓት ከተከወነ በኋላ ይሆናል። ከሥነ ስርዓቱ ስያሜ መፍታት የሚለው ቃል መውጣት፣ ከተለየ፣ ከታገደ፣ ከተከለከለ ነገር ነፃ መሆን የሚል ትርጉም ያለው ነው። የሟች ሚስት ወደ ማኅበረሰቡ መልሳ የምትቀላቀለው ግን በአዲስ ማንነት ነው፤ ሞት ከመከሰቱ በፊት ባለትዳር ሴት የነበረች ሲሆን ሞት ከተከሰተ በኋላ ግን ባሏን በሞት ያጣች ሴት ትሆናለች።

ከሞት በኋላ የሚደረጉ መታሰቢያዎችና ሶደቃም የሟችን ነፍስና የቋሚንም ህይወት መልክ የሚያስይዝ ነው። የሚደረገው ሶደቃ የሟችን ነፍስ መንገድ ያቀናል፣ ነፍስን ወደ መዳረሻዋ ያደርሳል፣ የሟች ነፍስ በዚያኛው ዓለም ተቀባይነት እንድታገኝ ይረዳል በሚል እምነት ምክንያት ይከወናል። ሶደቃ አለማድረግ ቋሚን ይረብሻል ተብሎም ይታመናል። ለሟች አለመሶደቅ የሟች ቤተሰብ መንፈስ እንዲረበሽ ያደርጋል፤ በሀገርም ላይ ድርቅን ወይም የበዛ ዝናብን ያስከትላል ተብሎ ይታመናል። በመሆኑም ቋሚ ሶደቃን በማድረግ ባለመሶደቁ ምክንያት ሊደርስበት የሚችልን መረበሽ ይከላከላል፤ ሥነ ልቡናዊ እፎይታን ያገኛል።

## 6. ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ ከአርጐባ ብሔረሰብ የህይወት ሽግግር ሥነ ስርዓቶች መካከል የለቅሶ ሥነ ስርዓትን ክዋኔ መተንተን ነው። የጥናቱን ዓላማ ለማሳካት የተዛማጅ ጥናቶች ክለሳ፣ የጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች ንባብ ተከናውኗል። የመስክ ስራ በማከናወን ቀዳማይ መረጃ የተሰበሰበ ሲሆን ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ዘዴዎች በመስክ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውለዋል።

የአርጐባ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥነ ስርዓት የመለየት ደረጃ አንድ ሰው በጽኑ ሲታመም ጀምሮ ታማሚው በህይወት እስኪያልፍ ድረስ የሚቆይ መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል። ይህ ጊዜ ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች በጠና ሲታመም ከሌላው ሰው ተለይቶ ይታያል፤ ቤተሰቡና የቅርብ የሆኑ ሰዎች ያስታምሙታል፤ የተለየ ምግብ ያዘጋጁለታል፤ ዱዓ ያደርጉለታል። ታማሚው ሲሞት ደግሞ ከዓለም ኑሮ ይለያል። ይህ በመሆኑ ሟች በሁለት የመለየት ደረጃዎች ያልፋል። ከሟች ቤተሰብ አንፃር ሲታይ የሟች ቤተሰብ የቤተሰቡ አባል በሞት በመለየቱ ምክንያት ሀዘንተኛ በመሆኑ ከእለት ተእለት ኑሮው የሚለይበት ጊዜ ነው።

የሽግግር ደረጃ ሞት ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ቆዳ ማጠፊያ ቀን ዋዜማ ድረስ ያለው ጊዜ ነው። ይህ የሽግግር ጊዜ ከሟች አንፃር ሲታይ ሟች ከገሀዱ ዓለም የተለየበት ነገር ግን ነፍሱ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ የማትደርስበት ሲሆን ሀዘንተኞች በሀዘንተኛነታቸው ምክንያት ቀደም ሲል ከነበራቸው

ህይወት ተለይተው ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎችን ብቻ እየተቀበሉ የሚቆዩበትና የመቀላቀያ ጊዜያቸው ገና የሆነባቸው ሆነው ይቆያሉ። በዚህ ምክንያት ሁለቱም በሽግግር ደረጃ ላይ ይሆናሉ።

የመቀላቀል ደረጃ ከቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት ክዋኔ ጀምሮ ከዚያ በኋላ ያሉ የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች የሚከወኑበትን ጊዜ በሙሉ ያጠቃልላል። ቆዳ ማጠፊያ የመጀመሪያው የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓት ሲሆን የሟችን ነፍስ ወደ ዘላቂ ማረፊያዋ የሚያደርስ፣ ሀዘንተኞችንም በመጠኑ ቀደም ሲል ወደነበራቸው የእለት ተእለት እንቅስቃሴ የሚመልስ ነው። ከቆዳ ማጠፊያ ሥነ ስርዓት በኋላ የሚከወኑ የሙት መታሰቢያ ሥነ ስርዓቶች የሟችን ነፍስ ወደተሻለ ማረፊያ ያደርሳሉ ተብለው ታምኖባቸው የሚከወኑና ሀዘንተኞችም እያንዳንዳቸውን መታሰቢያዎች ተከትለው ቀደም ሲል ወደነበራቸው ህይወት በተሻለ የሚመለሱባቸው በመሆናቸው ዋነኛ የመቀላቀል ደረጃ መገለጫዎች ናቸው።

በጥናቱ በክዋኔው ውስጥ ያሉ ድርጊታዊ (የታመመን ሰው በቀኝ ጐኑ ማስተኛት፣ ዳስ መጣል፣ ከመቃብር ስፍራዎች ላይ ዛፍ መቁረጥ ክልክል መሆን፣ ጥልፍ መተርተር፣ አስከሬን ላይ ሽቶ ማርከፍከፍ፣ ምግብ መመገብ፣ ውሀ ማርከፍከፍና እርጥብ ቅጠል መጐዝጐዝ፣ ባሏ የሞተባትን ሴት ሰውነትን ቅቤ መቀባትና አዲስ ቀሚስ ማልበስ፣ ቆዳን በጠዋት ማጠፍ፣ ቆዳ ላይ ውሃ ማርከፍከፍና ማጠፍ፣ ቆዳ መዘርጋትና ማጠፍ፣ እጅንና ፊትን በቀዝቃዛ ውሃ መታጠብ) እና ቁሳዊ (ውሀ፣ ቆዳ) ትዕምርቶችና ፍቺዎቻቸው ቀርበዋል።

የብሔረሰቡ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ተግባቦታዊ፣ ማኅበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር፣ ኢኰኖሚያዊና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑ በጥናቱ ተገልጿል። በብሔረሰቡ የለቅሶ ሥነ ስርዓት ሰዎች በለቅሶ ቤት በመገኘታቸውና በሚከወኑ ሥነ ስርዓቶች ላይ በመሳተፋቸው ሀዘንን እየተጋሩ መሆኑን እየገለፁ፣ ለሀዘንተኞቹ ያላቸውን ቅርበት፣ ፍቅርና አጋርነት እያሳዩ በመሆኑ ክዋኔው ተግባቦታዊ ፋይዳ አለው። ይኸው የሰዎች ተሳትፎና በለቅሶ ሥነ ስርዓት ላይ በጋራ መመገብ የሰዎችን አብሮነት የሚያስገኝ በመሆኑ ክዋኔው ማኅበራዊ ግንኙነትን የማጠናከር ፋይዳ አለው። ለቅሶ ደራሾች ለሀዘንተኞች የሚያደርጉት የገንዘብና የዓይነት ስጦታ ለሀዘንተኞች ኢኰኖሚያዊ ፋይዳን ያስገኛል። ለቅሶ የመድረስ ልማድ ደግሞ ሀዘንተኞች የሚከሰትባቸውን መረበሽ በመቀነስ ረገድ ለሀዘንተኞች ትልቅ ፋይዳ አለው፤ ሶደቃን ማድረግም ለቋሚ ሥነ ልቡናዊ እፎይታን ያስገኛል። የጥናቱን ግኝቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ተሰጥተዋል።

- ሀፊሻን የመሰለ የብሔረሰቡን እሴት ከዘመናዊ የመረዳጃ ተቋማት ጋር ማስተሳሰር ለቀጣይነቱ የራሱን አስተዋጽኦ ስለሚያደርግ የወረዳው የባህል ጽ/ቤትና በአካባቢው ያሉ ዘመናዊ የመረዳጃ ተቋማት ይህን ለማድረግ ጥረት ቢያደርጉ፣

- ዚያራ ለበርካታ ቀናት የሚከወንና ዝርዝር ክዋኔዎችንም የያዘ ሥነ ስርዓት ነው። በመሆኑም በፎክሎር እና አንትሮፖሎጂ የጥናት መስክ ያሉ ተመራማሪዎች በዝርዝር ቢያጠኑት፣

## ዋቢ መጻሕፍት


ለማ ንጋቱ። (2006)። *የለቅሶ ሥርዓት ክወና በደቡብ ጎንደር ዞን*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። (ያልታተመ)።

ሕይወት አበሩ። (2003)። *የመኢኒት ብሔረሰብ ባህላዊ የልቅሶ ሥርዓት ክዋኔ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

መሰለ ሙሉጌታ። (2010)። *የህይወትና ሞት እሳቤዎች በአክሱም የሞት ሥነ ስርዓት እና ንጻሬ ዓለም ውስጥ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። (ያልታተመ)።

__________። (2000)። *ባህላዊ የወሊድና የገለብ ሥነ ስርዓት ፎክሎራዊ ክዋኔ በአክሱም የክርስትና እምነት ተከታዮች*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ሞገስ ሚካኤል። (2002)። *በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣ በሥርዓቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

*ሥራየ* እንዳለው። (2023)። የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማኅበረሰብ። *Journal of Afro-asiatic Languages, History and Culture,* 12(1), 106-123.

___________። (2005)። *የህይወት ዘመን ዑደት ሽግግር ደረጃዎች ስርዓተ ክዋኔ በፍኖተ ሰላም አካባቢ ከፎክሎር ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ አንፃር*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

*አህመድ መሀመድ ኢብራሂም*። (1999)። *በኢትዮጵያ የማክዙማይትና የሃሺማይት ወላስማ ስርው-መንግስት ስልጣኔና ታሪክ የአርጐባ ሕዝብ የመነሻና የማንነት ግንዛቤ።*

አበባ አማረ፣ ደስታ አማረ እና ፍሬህይወት ባዩ። (2015)። የሕይወት ኡደት ባህላዊ ክዋኔና ሥርዓት በስልጤ። *Some Features of Diversity of Ethiopian Languages and Cultures*. Vol. 2, Addis Ababa University, Addis Ababa University business enterprise printing press. 2-115.

አየሁሽ ቶማ። (2005)። *የወላይታ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ-ክዋኔ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

አዲሱ ጴጥሮስ። (2000)። *የአርጐባ ማኅበረሰብ የማንነት ቃላዊ ዝርው ተረኮች ትንተና*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

አፀደ ተፈራ። (2007)። *የዋግኽምራ የወሊድ የጋብቻ እና የሞት ሥኑ-ሥርዓት ፋይዳ ትንተና*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። (ያልታተመ)።

ኤልሳቤጥ ጥበቡ። (2010)። *የወርጂ ብሔረሰብ የጋብቻ ስርዓት*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

እታገኘሁ አስረስ። (2010)። የአርጎባ ብሔረሰብ አፋዊ ትውፊቶችና መገለጫዎች ጥበቃ ጥናት። *የአራተኛው አገር አቀፍ የባህል አውደ ጥናት መድበል*። ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ። 143-173።

ውቤ ታደገ። (2005)። *የቤንች ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ዐቢዩ አስማማው። (2005)። *የአርጎባ ብሄረሰብ የቤት ውስጥ መገልገያና የማጌጫ ቁሶች፣ በአማራ ክልል ደቡብ ወሎ ዞን፣ አርጎባ ልዩ ወረዳ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር መርሀ ግብር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ዘላለም ፋንቱ። (2004)። *የለቅሶ ሥነ-ስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ዝናሽ ሰለሞን። (2004)። *የሀድያ ብሔረሰብ ባህላዊ ጋብቻና የሠርግ ሥነ ስርአት*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

የአርጐባ ልዩ ወረዳ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት። (2010)። *በአፋር ብ/ክ/መንግስት የአርጐባ ልዩ ወረዳ*። SSB ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ። (2006)። *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማተሚያ ቤት።

ደስታ አማረ። (2007)። *የህይወት ኡደት (የወሊድ፣ የጋብቻና የሞት) ስርዓቶች ክዋኔ ትንተና በወሊሶ ሊበን ኦሮሞ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በፎክሎር መርሃ ግብር የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት። (ያልታተመ)።

ደስታ ወ/መስቀል። (2006)። *የዲዚ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓተ ክዋኔ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ድርብወርቅ ብፁ። (2007)። *የጉምዝ ብሔረሰብ ዋና ዋና የሕይወት ዘመን ኡደት ሽግግር ደረጃዎች ሥርዓት በማንዱራ ወረዳ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

ፍፁም ብርሃኑ። (2006)። *የሸካቾ ብሔረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርዓት ክዋኔ*። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ሥነ ጽሁፍና ፎክሎር የኤም.ኤ ዲግሪ ለማግኘት ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጥናት። (ያልታተመ)።

Aklilu Asfaw. (2000). A Short History of the Argobba. *Annals d'Éthiopie*. XVI, 173-183.

Barnard, A. and Jonathan Spencer. (1996). rite of passage. *Encyclopedia of Social and Cultural Anthropology*. London, Routledge, 737-738.

Bauman, R. (2012). Performance. *A Companion to Folklore*. Regina F. Bendix and Galit Hasan-Rokem (eds.). Blackwell Publishing Ltd, 94-118.

____________. (1975). Verbal Art as Performance. *American Anthropologist.* 77.2: 290-311.

Bell. C. (1997). *RITUAL Perspectives and Dimensions*. Oxford: Oxford University Press.,

Bronner, S. J. (ed.). (2007). *The Meaning of Folklore the Analytical Essays of Alan Dundes*. Utah, Utah State University press.

Feinberg B. (2004). Passage, Rites of. *Encyclopedia of Religious Rites, Rituals, and Festivals*. New York. Routledge, 311-314.

Finnegan, R. (1992). *Oral Traditions and The Verbal Arts a Guide to Research Practices*. London, Routledge.

Gennep, A. V. (1960). *The Rites of Passage*. Chicago: University of Chicago Press.

Gerhart, k. M. (2009). *The material culture of death in medieval Japan*. U.S.A. University of Hawaii press.

Grimes, R. L. (2000). *Deeply into the Bone Re-inventing rites of Passage*. London, University of California Press.

Ismaiel, M.I. (1997). *Sahîh Al- Bukhâri*. Trans. Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 1. Darussalam.

________. (1997). *Sahîh Al- Bukhâri*. Trans. Khan, Muhammad Muhsin. Vol. 2. Darussalam.

Leslau, W. (1973). *English-Amharic Context Dictionary*. Otto Harrassowitz. Wiesbaden.

Lobar, S. L. JoAnne M. Youngblut and Dorothy Brooten. (2006). Cross-Cultural Beliefs, Ceremonies, and Rituals Surrounding Death of a Loved One. *Pediatric nursing*. 32(1), 44-50.

Malinowski, B. *A Scientific theory of Culture and other Essays*. The University of North Carolina Press.

Pentikäinen, J. (1997). Rites of passage. *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Thomas A. Green (ed.). Santa Barbara, ABC-CLIO, Inc. 732-733.

Radcleffe-Brown, A. R. (1952). *Structure and Function in Primitive Society*. Glencoe, The Free Press.

Rappaport R. A. (1992). Ritual. *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entertainments.* Richard Bauman (ed.). Oxford, Oxford University Press, 249-260.

Seid Muhie. (2015). *Documentation and Description of the Rekebot Traditional Conflict Resolution System of the Argoba Community*. Addis Ababa University. Presented in partial fulfillment for the requirements for the degree of Master of Arts in Documentary linguistics and Culture. (unpublished).

Shujaa, M. J. (2009). Rituals. *Encyclopedia of African Religion.* California, SAGE Publications, Inc., 575-579.

Sims, M. C. and Martine Stephens. (2005). *Living Folklore An Introduction to the Study of People and Their Traditions*. Utah. Utah State University Press.

Storey, J. *Cultural Theory and Popular Culture An Introduction*. London. Pearson Longman.

Tesfaye Hailu. (2000). History and Culture of the Argobba. *Annales d'Ethiopie*. XVI, 195-206.

*The Quran*. (2005). Translated by M.A.S. Abdel Haleem, Oxford university press.

Turner E. (1997). Anthropology, Symbolic. *FOLKLORE: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. Santa Barbara, ABC-CLIO, Inc., 25-29.

Turner, V. (1975). Symbolic Studies. *Annual Review of Anthropology*. 4: 145-161.